

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER
ይቻላል
It's Possible!



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# ንግድና ልማት

ሚያዝያ 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## የደቡብ አፍሪቃ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት አላቸው ተባለ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ 11 የደቡብ አፍሪቃ ባለሃብቶች በአዲስ አበባ ተገኝተው ከኢትዮጵያዊያን የንግድ ህብረተሰብ አባላት ጋር በጋራ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ የደቡብ አፍሪካ ኢምባሲ የሁለትዮሽ ግንኙነት ኃላፊ ሚስስ ታምራ ናዳባ የንግድ ለንግድ ግንኙነቱ ሲጀመር እንዳሉት ፤ ሀገራቱ ጠንካራ የሚባል ወዳጅነት ያላቸው ቢሆንም ወደ ንግድ ማሳደግ አልቻሉም ብለዋል ፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል > >>

## ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ሀገራዊ ስጋት እንደሆነ ተገለጸ

**በትንሹ በአመት ወደ 3 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ይወጣል፤ ይህም ከአመታዊ የኤክስፖርት ገቢያችን ጋር ይስተካከላል፡፡**

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት ያስጠናው አንድ ጥናት እንዳመለከተው በሕገወጥ /በኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ከአገር የሚገባውም ሆነ የሚወጣው የገንዘብ ሃብት በአገሪቱ እድገት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እያሳረፈ ነው ይላል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል > >>

## የውጪ ምንዛሬው በገበያ ከመሆኑ በፊት ቀዳሚ ሥራዎች አሉ፡፡



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በያዝነው የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከኤክስፖርት የተገኘው 1 ቢሊዮን ዶላር ፤ በዚሁ ጊዜ ለኢምፖርት 4 ቢሊዮንሊ ዶላር ወጥቷል፡፡ 3 ቢሊየኑ ከየት መጣ ?

ወደ ገጽ 8 ዞሯል > >>



## አዲስ ቻምበር የቢዝነስ ማበልፀጊያ ማዕከሉን ( BIC) ፕሮጅክት ይፋ አደረገ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

ማዕከሉ ለስራ ፈጣሪዎች የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመሰጠት ሥራ ፈጣሪዎች የቢዝነስ ስራቸውን እንዲያሳድጉና እንዲያስፋፉ በማለም የተቀረፀ መሆኑን በይፋ ማድረጊያ ስነ-ስርዓቱ ላይ ተገልፃል፡፡

ወደ ገጽ 10 ዞሯል > >>

MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ.የተ.የግ.ማህበር

Elfora Agro Industries P.L.C.
A Member of the MIDROC Investments Group Companies



ELFORA STANDS FOR NATURAL & QUALITY PRODUCTS !

Phone: +251-116-46-10-79, +251-116-45-03-61
Fax: +251-116-45-05-03
E-Mail: elforamarketing@gmail.com
mohzeki73@gmail.com
Website: midrocinvestmentgroup.com/en

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
እስራኤል ማንአየ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ሚያዝያ 2015 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## የተሻለ የፋይናንስ አቅራቦት ለጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች

በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈጣሪዎች እና የቢዝነስ ተቋማት ንግድ ለመጀመር ይሁን የንግድ ሥራቸውን ለማስፋፋት እንዲሁም አቅማቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። የፋይናንስ አቅራቦት እጥረት የንግዱ ማህበረሰብ የንግድ ማነቆ ብሎ ከጠቆማቸው ውስጥ 40 በመቶውን ይይዛል። እንደ ዓለም ባንክ 2021 ንግድን የመስራት ሪፖርት ኢትዮጵያ ከ190 ሀገራት መካከል ለንግድ የሚውል ብድርን በማግኘት ረገድ 176ኛ ደረጃን ይዛለች።

እ.ኤ.አ በ2014 ሀገሪቱ ንግድን ለመስራት እንቅፋት ከሆኑ ተግዳሮቶች መካከል የፋይናንስ አቅራቦት ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ በ2019 የሀገር አቀፍ ቢዝነስ አጀንዳ አምስተኛው ዋነኛ ተግዳሮት ነበር። እንደ 2020/21 የዓለም-አቀፉ ተወዳዳሪነት ሪፖርት የገንዘብ አቅራቦት ከውጪ ምንዛሬ አሰጣጥ ደንብ እና ሙስና ቀጥሎ ሶስተኛው ዋነኛ ችግር ሆኖ ተቀምጧል።

በኢትዮጵያ ያሉ ንግድ ባንኮች፣ የልማት ባንክ እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ለንግድ ኩባንያዎች ዋነኞቹ የብድር አቅራቢዎች ናቸው። ምንም እንኳን በእነዚህ የሚቀርበው የብድር መጠን ላለፉት አምስት አመታት በመጠን ረገድ ቢለያይም ባንኮቹ አሁንም ለደንበኞቻቸው አጭር እና የረጅም ጊዜ ብድር እየሰጡ ይገኛሉ።

ከግል ባንኮች አንጻር ሲወዳደር በመንግስት ይዞታነት በሚተዳደሩት በተለይም የኢትየጰያ ልማት ባንክ በኩል የሚቀርበው የብድር መጠን ዳጎስ ያለና የረጅም ጊዜን ማዕከል ያደረገ እንደሆነ ይታወቃል።
መደበኛ የፋይናንስ ተቋማት በተለይም የግል ባንኮች የሚሰጡት የብድር መጠን አነስተኛ የሚባልና በቅድመ ሁኔታዎች የተወሳሰበ ነው። በመሆኑም የንግድ ድርጅቶች በገንዘብ እጦት በሙሉ አቅማቸው ለመስራት ሲቸገሩ ይስተዋላል። አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶች ለማቅረብ እና ተወዳዳሪ ለመሆንም እንቅፋት ሆኗቸዋል።

በቂ ያልሆነ የብድር መጠን፣ ብድር የሚከፈልበት ጊዜ በእጅጉ ማጠር፣ ትልልቅ የብድር መያዣና ቅድመ ሁኔታ፣ የግልጽነት አለመኖር፣ የብድር መክፈያ ምጣኔ ከፍተኛ መሆን፣ ብድር ለማግኘትና ለማስፈቀድ ረጅም ጊዜ መውሰዱ እና የብድር አይነቶች በአይነት ረገድ አለመስፋት በተበዳሪዎች ላይ ትልቅ ተግዳሮትን ፈጥሯል።

በመሆኑም የገንዘብ አቅራቦትን ለማስፋት የግል ካፒታል ገበያን መመስረትና የገንዘብ አቅምን ማሳደግ ይቻላል። ይህ ደግሞ የውጪ የፋይናንስ ተቋማት እና በውጪ የሚኖሩ ዜጎች ያላቸውን ሀብት በማንቀሳቀስ የፋይናንስ አቅም እንዲዳብር መንገድ ይከፍታል። የውጪ ሀብትን መጠቀም የሚያስችል የኢኩዩቲ ካፒታል አሰራር መዘርጋት እና ትክክለኛ እና ተመጣጣኝ የወለድ ምጣኔ ያለው የሊዝ ፋይናንስ ብድር ማእቀፍን እውን ማድረግ ይገባል።

ባንኮች በዓመታዊ የብድር ድልድላቸው እና አሰጣጣቸው ለኢኮኖሚው እድገት ሞተር ለሆነው የግል ዘርፍ የተወሰነ መጠን ኮታ እንዲሰጥ እቅድ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አሁን እየታየ ያለው 80 በመቶ ብደር እየቀረበ ያለው ለመንግስት መሆኑ ችግሩን ያጎላዋል። ስለሆነም የፋይናንስ ተቋማት ለቢዘነስ አንቀሳቃሾች በቂ ብድር ማቅረብ አለባቸው። በጠቅላለው ግልጽነትን ማሳደግና የብድር አቅራቦት መጠንን ማሻሻል ለነገ የሚተው ጉዳይ አይደለምና።

የብድር መያዧ ቅድመ ሁኔታዎችን በተወሰነ ደረጃ ማላላት የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ አንዳንድ የንግድ ተቋማት እንደ ፕሮጀክት አይነታቸውና የፋይናንስ አስተዳደራቸው እንዲሁም በማምረት ላይ የሚገኙ ኩባንያዎችን ከብድር መያዣ ግዴታ ነጻ ቢሆኑ ጠቃሚ ይሆናል።

ለጀማሪ የቢዝነስ ስራ ፈጣሪዎች እንደ ፕሮጀክት ሃሳባቸውና አዋጪነቱ በተመጣጣኝ የወለድ ብድር ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህ ጉዳይ ባንኮች ጠንካራ ክትትልና ግምገማ ቢያከናውኑ ይመረጣል። ከዚህ በተጨማሪ የብድር መረጃና ምዝገባ ቢሮ/ተቋም/ ማቋቋምና ማጠናከር አንዱ ሲሆን የአእምሮ ንብረት ባለቤትነትን እንደ መያዣ መውሰድና የግልና የመንግስት ትብብርን በማጠናከር ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ብሎም ልማትና እድገትን ማረጋገጥ ይበጃል።

# በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የወጣት ስራ ፈላጊዎችን ጥያቄ ለመመለስ ሁሉም ባለ ድርሻ ሊረባረብ እንደሚገባ ተገለጸ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

የተቀናጀ የወጣቶች ፕሮጀክት ወይንም ከፍታ በስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ ላይ የንግድ ለንግድ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር ልዩ አማካሪ ነቢያ መሀመድ በኢትዮጵያ የወጣቱ የህብብረተሰብ ክፍል ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥር ይይዛል ፤ ይህውም 70 ሚሊየን ይሆናል ብለዋል ፡፡ ወጣቱ ትልቅ ሀብትና አቅም መሆኑን ጠቁመው ይህንን የወጣት ሃይል በአግባቡ ከተጠቀምንበት ትልቅ ሃብት ነው ብለዋል ፡፡

ለዓመታት ለወጣቶች የሚፈጠር የስራ እድል አልነበረም ያሉት ነቢያ፤ ይህም ሊሆን የቻለው ሀገሪቱ ካለችበት ድህነትና ኃላቀርነት እና ተያያዥ ምክንያቶች የስራ አጡ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ሊሆን ችሏል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በየአመቱ 2 ሚሊየን ወጣት ስራ ፈላጊ ወደ ገቢያው እንደሚገባ አንስተው ፤ ይህንን ስራ ፈላጊ ወጣት ወደ ስራ ካላስገባነው እድል ሳይሆን ጥፋት ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡

መንግስት ይህንን ወጣት ወደ ስራ እንዲገባ ኃላፊነትም ግዴታም አለበት ያሉት ወ/ሮ ነቢያ የግሉ ዘርፍ የበለጠ ሚና መጫወት ይኖርበታል ሲሉ አሳሰበዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው በያመቱ 3 ሚሊየን ስራ ለወጣቱ ለመፍጠር ግብ አስቀምጠን ወደ ስራ ገብተናል ያሉት አማካሪዋ ወ/ሮ ነቢያ ፤ ይህውም ገበያው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ከማዘጋጀት ጀምሮ ፤ የሚፈጠረው የስራ እድል ዳቦ መብላት መሆን አለበት ብለን እየሰራን ነው፡፡ ሆኖም የብድር አቅርቦት ፣ የገቢያ ትስስር ፣ የመስሪያ ቦታ ፣ የመሸጫ ቦታ ችግሮች ትልቅ ክፍተት መሆናቸውን ጠቅሰው ፤ ይህንን ችግር ለመፍታት የስራና ክህሎት ሚንስቴር የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርፆ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በግሉ ዘርፍና በመንግስት መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ በመሆን የግሉን ዘርፍና የማህበረሰቡን ጉዳዮች በማንሳት ግንዛቤ ማሳደግ የንግድ ለንግድ ትስስር በመፍጠር ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ለአነስተኛና ጥቃቅን ልምድ ማካፍልና ማብቃት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በሀገራችን ስራ ፈጣሪዎች ሲመሩ ቆይተው ፤ ለወጣቱ የማስተላለፍ ነገሮች ቢኖሩም ወጣቱ በእውቀትና በክህሎት ሳይዘጋጅ ድርጅትን እንዲመራ ድርጅቱን ለውድቀት መዳረጉ አይቀሬ ነው ያሉት አቶ ዘካሪያስ አሰፋ የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሀፊ ፤ በዚህም ምክንያት ስኬታማ የተባሉ የቢዝነስ ሰዎች ለልጆቻውም ሆነ ለሌሎች ስራተኞች ኃላፊነታቸውን ካስተላለፉ በኃላ ስኬታማ መሆን ተስኖት ሲወድቅ ይታያል ብለዋል፡፡

በመሆኑም ወጣቱን በማነፅ ፣ ድርጅት የመምራት ብቃቱ እንዲጎለብት የማብቃት ስራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ምክር ቤቱ ወጣትና ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከል ፕሮጀከት ይፋ ማድረጉን ጠቅሰው፤ ስልጠናዎችን መሰጠት ፣ የገቢያ ትስስር መፍጠርና የስራ ፈጣሪነት ባህልን ማሳደግ እንዲሁም ስራ ፈጣሪዎች ያለባቸውን የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ ፕሮጀክቱ ወደ ስራ መግባቱን ገልፀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ አገሪቱ ማሳካት የምትፈልገው ከዘላቂ ልማት ጋር የተጣጣመና የስራ ፈጠራና የቢዝነስ-ምህዳሩን ለማሰፋት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የተቀናጀ የወጣቶች ፕሮጀክት በስራ እድል ፈጠራ ፣ በኢኮኖሚ እገዛ ፣ በጤና ፣ በሲቪክ እና ለወጣቶች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በ18 ከተሞች ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡
በወጣቶች ንቁ ተሳታፊዎች ላይ የሚሰራው ይህ ፕሮጀክት ለአምስት አመት የሚቆይ ሲሆን ከመንግስት እቅድና ኢንቨስትመንት ጋር የተጣመረ ነው ብለዋል ፡፡

በወጣቶች የሚመሩና የሚተዳደሩ ቢዝነሶችን ለመደገፍ የሚያስችሉ በርካታ የፕሮጀክት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡ የንግድ ትስስር መድረክ ለቢዝነስ ጀማሪ ወጣቶች እንዲሁም ቢዝነስ ለመጀመር ሃሳብ ላላቸው ወጣቶች ልምድና ተሞክሯቸውን አካፍለዋል፡፡

በንግድ ለንግድ ትስስርና ውይይት መድረኩ ላይ በዶሮ እርባታ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ፣ በቆዳና ሌጦ ዘርፍ ፣ የተሰማሩ ስኬታማ ወጣቶች ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡
የንግድ ለንግድ መድረኩ ዋና አላማም ሞዴል የቢዝነስ ድርጅቶችና ወጣቶች መካከል ግንኙነት እና ትስስር ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡

እንደዚሁም የወጣቶችን የስራ እድል ለይቶ ለማወቅና ለገቢያ ቅልጥፍና አስተዋፆ በሚሆን መልኩ ወጣቶች የራሳቸውን ስራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ጭምር መሆኑን በመድረኩ ላይ ተገልፃል፡፡

# የደቡብ አፍሪቃ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት አላቸው ተባለ

ሁለቱ አገራት የሁለትዮሽ ንግድ ግንኙነትም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያነሱት ሚስስ ታማራ ለዚህም እንደ ማሳያ ያነሱት የሁለቱ አገራትን የንግድ ልውውጥን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከደቡብ አፍሪካ 525 ሚሊየን የደቡብ አፍሪካ ራንድ ምርት ስትሸምት ፤ 225 ሚሊየን ራንድ የሚያወጣ ምርት ትልካለች ብለዋል፡፡

በመሆኑን ይህንን የንግድ ልውውጥ አሁን ካላበት የበለጠ ለማሳደግ መስራት ያስፍልጋል ብለዋል፡፡
አክለውም በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የተደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ከተደረገባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የቴሌኮም ዘርፍ አንዱ ነው፡፡

የወጣውን ጨረታ አሸንፎ ወደ ገበያ ከገባው ሳፋሪኮም የቴሌኮም ኩባንያዎች ስብሰብ ውስጥ መካከል አንዱ ቮዳፎም ኩባንያ 6 ነጥብ 2 በመቶ ድርሻ እንዳለው ጠቅሰዋል፡፡

የባንክን ዘርፉ ነፃ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት ይፋ ማድረጉን ተከትሎ ፤ ደቡብ አፍሪካ የባንክ ኢንዱስትሪ ላይ የሚሰሩ ኩባንያዎች ዘርፉን ለመቀላቀል ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

የአዲስ ቻምበር ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ዘካሪያስ አሰፋ በበኩላቸው ምክር ቤታቸው ከደቡብ አፍሪካ ኢምባሲ ጋር መልካም ግንኙነት እንዳለው ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም የሁለቱ አገራት ንግድ ግንኙነት እንዲጠናከር እንደሚሰራ ጠቅሰው ፤ የደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያሉ የንግድ እድሎችና አብረው መስራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ማብራሪያዎችን ኢምባሲው ለምክር ቤቱ አባላት እየሰጠ መሆኑን ለማሳያነት አቅርበዋል፡፡

የኬፕ ታውን ከተማ ባለሃብቶችን ያቀፈውን የንግድ ሉዕካን የመሩት የከተማዋ ቱሪዝም ፣ ንግድና ኢንቨስትመንት የዌስግሮው ኃላፊ ሚካኤል ጋምዎ በበኩላቸው ዓላማቸው የንግድ ትስስሩን ማጠናከር ነው ብለዋል፡፡

የደቡብ አፍሪካ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ መዋለንዋያቸውን እንዳፈሰሱ አስታወሰው ፤ የበለጠ ስራ በመስራት ሁለቱም አገራት ሊጠቀሙ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ የሉዕካን ቡድኑ መሪና የኬፕ ታውን እና ምዕራብ ኬፕ ብሄራዊ የቱሪዝም፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የፊልም ማስተዋወቅ ኤጀንሲ (ዌስግሮው) ኃላፊ ማይክል ጋሞው መዋለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚፈልጉ በርካታ የደቡብ አፍሪካ ባለሃብቶች እንዳሉ ጠቅሰዋል፡፡

ሆኖም በሀገሪቱ ያለው የንግድና እና ኢንቨስትመንት አማራጮች እንዲሁም ኢትዮጵያዊያን ባለሃብቶች እንዴት ብንሰራ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን የሚለውን ለመወያየትና ለመምከር 11 አባላት ያሉትን የንግድ ሉዕካን እየመሩ አዲስ አበባ መገኘታቸውን ገልፀዋል፡፡

በንግድ ለንግድ ውይይቱ ላይ በግብርና ቢዝነስ መስክ ፣ በኮንስትራክሽን ( ግንባታ ) ማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲሁም ቱሪዝም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች አብረው መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መክረዋል፡፡

# የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከላት ለዕድገት ያላቸው ሚና

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከል አቋቁሞ ለምረቃ አብቅቷል፡፡ ሚያዝያ 16/2015ዓም በካፒታል ሆቴል የማዕከሉ ይፋዊ ሥራ ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፤የንግድ ም/ቤቱ መሪዎች ፤አንጋፋ የቢዝነስ ሰዎች ፤ተባባሪ ወገኖች እና ሌሎች ባለድርሻዎች ተገኝተዋል፡፡ በዝግጅቱ ላይ በወጣቶች ሥራ ፈጠራ መስክ ሰፊ ልምድ እና ዕውቀት ያላቸው ምሑራንን ያሳተፈ አንድ የውይይት መድረክ ተካሂዶ ነበር፡፡ እኛም ለአንባቢያን በሚመች መልኩ አሳጥረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል ፡፡

"የቢዝነስ ማበልጸጊያዎች በመንግሥት፤ በትምህርት እና በምርምር ተቋማት፤በግሉ ዘርፍ መካከል ጠንካራ ቁርኝት እንዲፈጠር ያግዛሉ፡፡"

አቶ ባሕሩ ዘይኑ (የአፍሪኮም ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ)



ከ25 አመታት በላይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሰማሩት እና አፍሪኮም ኩባንያ ባለቤት የሆኑት አቶ ባሕሩ ዘይኑ አንዱ ተናጋሪ ናቸው፡፡ የማበልጸጊያ ማዕከላት ለሥራ ፈጠራ ባሕል እንዲያድግ ስላላቸው አስተዋጽኦ አስመልክተው በሰጡት አስተያየት ማዕከላቱ ሥራ ለጀመሩም ሆነ ለጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች እርስ በእርሳቸው እንዲተዋወቁ ፤የገበያ መረጃዎች እንዲለዋወጡ፤ የቢዝሰነስ ትስስር እንዲፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ ብለዋል፡፡ በአዲስ አበባ በሚገኘው የአይ.ሲ.ቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያለውን ተሞክሮ በምሳሌ አንስተው ሲናገሩ በዚያ ወደ ማበልጸጊያዎች በየቀኑ በርካታ የውጪ እና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ይመጣሉ፡፡

ይህ አጋጣሚ በፓርኩ ውስጥ ላሉ ጀማሪ ወጣቶች በቀላሉ ከነብኚዎች ጋር እንዲተዋወቁ ዕድል ይሰጣል ፤ ቀጥሎም የውጪ እና አገር ውስጥ ገበያዎችን በቀላሉ አፈላልገው እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፓርኩ ውስጥ የሚሰጡ በርካታ ስልጠናዎች አሉ፡፡

ለጀማሪዎች ሌላው ዕድል በዚያው ከፓርክ ውስጥ ባንኮች ስለሚገኙ ብድር ለማግኘት ዕድል ያገኛሉ ብለዋል፡፡ የቢዝነስ ማበልጸጊያዎች የሥራ ፈጠራ ባሕል እንዲስፋፋ ያላቸው ተጨማሪ አስተዋጽኦ በመንግሥት፤ በትምህርት እና በምርምር ተቋማት እና በግሉ ዘርፍ መካከል ጠንካራ ቁርኝት እንዲፈጠር ያግዛሉ፡፡ ለምሳሌ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች የእውቀት እና የክህሎት ጉድለት ሲያጋጥማቸው ከኮሌጆች እና ከዩኒቨርሲቲዎች በሚደረግላቸው ትብብር በቀላሉ ችግራቸውን መቅረፍ ይችላሉ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉት ምቹ ሁኔታዎች አደዲስ ሥራ ፈጣሪዎች እንዲበዙ እና የጀመሩትም እንዲያድጉ የቢዝነስ ማዕካለት ሁነኛ አስተዋጽኦ አላቸው ፡፡ የአገራችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያለው በሚመጣው ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ላይ ነው የሚሉት አተ ባሕሩ ፡፡ ጀማሪዎች ሲበዙ ፤የሥራ ዕድሎን ያበዛሉ፤ የሥራ ዕድሎች ሲበዙ አጣቃለይ ኢኮኖሚችን ያድጋል፡፡ ይህንን አስበን በትክክል ካልሰራን የአገራችን ወደፊት ስጋት ይሰማኛል ብለዋል፡፡ በአጠቃላይ በአገራችን የሥራ ፈጣሪነት ባሕል እንዲስፋፋ የሥራ ፈጠራ ዘርፍ ላይ ያሉ ንግድ ምክር ቤቶችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻዎች በጠንካራ ትብብር መንፈስ ተጋግዘው ዘርፉን ማሳደግ አለባቸው ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

"ማበልጽጊያ ማዕከላት በጥናት የተደገፈ የፖሊሲ ማሻሻያዎቸን ማፍለቅ ይችላሉ"

(አቶ ስመኝ ታደሰ የአርማዳ አግሪቴክ ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ)



አቶ ስመኘ ሌላው ተናጋሪ ሲሆኑ ከረዥም የሥራ ልምዳቸው እና ዕውቀታቸው በመነሳት የማበልጸጊያ ማዕከላት አስመልክተው ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ ተመሳሳይ ዝንባሌ እና ሰርቶ የመለወጥ ፍላጎት ያላቸው ወጣቶች በአንድ ቦታ እና ጊዜ የሚሰበሰቡበት እና ሃሳብ ለሃሳብ የሚለዋወጡበት ምቹ ቦታ ቢኖር የማበልጸጊያ ማዕከላት ብቻ ናቸው ይላሉ፡፡ ዛሬ ላይ የትላልቅ ኩባንያዎች ባለቤቶች መነሻቸውን ሰንጠይቅ የሚሰጡት መልስ ቢኖር የማበልጸጊያ ማእከላት ናቸው፡፡

የጀማሪዎች ቁጥር በእጅጉ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ነው፡፡ በመሬት ላይ ያለውም ሀቅ ይኸው ነው ይላሉ፡፡ ይሄ ችግር ጥናት ያስፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም ጀማሪዎች በተሰማሩበት ዘርፎች ላይ ያሉትን ችግሮች በደንብ ለይተን መፍትሔ እንድናስቀምጥ ይረዳናል፡፡ ዋናው ችግር ስለ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ሚያወራ መረጃም ይሁን የተጠናከረ የመረጃ ቋት የለም ብለዋል፡፡ ስለዚህ አንዚህ ያሉ የመረጃ ክፍተቶች ለመሙላት የማበልጸጊያ ማዕከላት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ስለዚህ ማዕከላቱ የጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎቸን እንቅስቃሴ እየተከታተሉ እና መረጃዎችን እየሰበሰቡ እና ጥናቶችን እየካሄዱ ለመንግሥት ፖሊሰ ማሻሻያ ግብአቶችን ማቅረብ ይችላሉ ሲሊ የቢዝነስ ማዕካለትን ሚና አሳይተዋል፡፡ ዛሬ ላይ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከላት የሚሰጡት እንደ ቢዝነስ ፕላን፤ቢዝነስ ሞዴል ወዘተ የመሳሰሉት ስልጠናዎች እንዳለ ከውጪ የተቀዱ ናቸው፡፡ ጀማሪዎች በቅ ብለው ወዲያው ይሚጠፉበትን ምክንያቶች መርምረን ከዚያም እያንዳንዱ ባለድርሻ ደግሞ የሚጠበቅበትን ምላሽ በመስጠት ማዕከላቱ የተሻሉ ስልጠናዎችን እንደሰጡ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ምክረሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ በተግባር ከታዘቡት በመነሳት ለጀማሪ ቢዝነሶች መዳከም ሌላው ምክንያት ሲገልጹ ራሳቸው ጀማሪ ወጣቶች በቢዝነስ ማበልጸጊያዎችን አስፈላጊነት ላይ ያላቸው እምነት ዝገቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ አብዛኞቹ ማዕከላቱ አያስፈልጉም የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ በአገራችን በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ማዕከላት የሚሰጡት ስልጠናዎች ተመሳሳይ መሆናቸው፤ የሚከተሉት ከሪኪዩለም ተመሳሳይ በመሆኑ ፤ ወጣቶቹ በቶሎ እንዲሰላቹ እና ሰልጠናዎችን እንዲተው ይገፋፋቸዋል ስለዚህ እያንዳንዱ ማበልጸጊያ ማዕከል የየራሱ ከሪከዩለም እኛ የሥልጠና ፍልስፍና ሊኖረው ይገባል ፡፡ ይሄ አካሄድ ለጀማሪዎች ሰልጠናዎችን መርጠው በፍላጎታቸው እንዲወስዱ ያስችላቸዋል ሲሉ ሳባቸውን አካፍለዋል፡፡

"ጥዋት ከእንቅልፋችን ስንነቃ ስለ ወጣቱ ማሰብ ያለብን ይመስለኛል"

(ዶ/ር ሐሰን ሑሴን የ ኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ)



አሁን ያለው ወጣት ትውልድ ከቀድሞዎቹ በተሻለ እና በተመቻቸ ጊዜ ላይ ነው ያለው፡፡ አዳዲስ ነገሮች ማወቅ ይፈልጋል ፤ የቴኖሎጂው እድገት እና የወጣቱ የዕውቀት ፍላጎት ንጻር ወጣቱ አሻራውን የሚያሳርፍበት ሥራ ዕድል አለ ለማለት አይቻልም፡፡ አሁን ወጣቱ የተሰማራበት ሥራ በአብዛኛው ሕይወትን ለመግፋት ያህል ነው፡፡ የቅርብ መረጃዎቸ እንደሚጠቁሙት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ የወጣት ቁጥር አለ፡፡ በግሉ ዘርፍ ደግሞ በጣም አናሳ ነው፡፡ ይሄ አንድ በግልጽ የሚያሳየን እውነታ አለ፡፡ ይኸውም የግሉ ዘርፍ መቀጨጨን እና በጣም አናሳ የሆነ ቁጥር ብቻ ለመሸከም መቻሉን ያሳያል ሲሉ ሲ ዶ/ር ሐሰን ሁሴን ይሞግታሉ ፡፡ በእርሳቸው ግምት የቢዝነስ ማዕከላት እንደ አሸን ቢበዙ ሰፊ መሠረት ያለው የግል ዘርፍ እስካልተፈጠረ ድረስ የሥራ አጥ ቁጥሩን መቀነስ አይቻልም፡፡ የሥራአጡ ቁጥር ወደፊቱ ስጋት አለያም ተስፋ ሊሆን ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ የማበልጸጊያ ማዕከላት መኖር አስፈላጊነቱን ማመን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አዲስ ቻምበር የጀመረውን ሥራ ሌሎችም ሊከተሉት ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር ሁለት ስለት አንዳለው በላዋ ማየት ያስፈልጋል ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ መንግሥት በሚሊዮኖች የሚቀጠሩ አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎች እንዲፈጠሩ ቢዝነስ ማህዳሩን ምቹ ማ እነዲሁን ሰፊ ሥራ መሥራት አለበት፡፡ የወጣቱን ቁጥር አንደ ችግር ሳይሆን አንደ ዕድል ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ አሁን ላለው ወጣት ምቹ ስነ ምህዳር ከጠርንለት ፤ በቂ ድጋፍ አድርገንለት ይህቺን አገር ወደ እድገት ይዞ የሚወጣ ነው፡፡ ነገር ግን በአገራችን ቢዝነስ ምቹ ሁኔታ አለ ወይ ? የሚለው ጥያቄ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጀማሪ ወጣቶች የሚያጋጥማቸው 3 ዋና ዋና ችግሮች አሉ፡፡ 1ኛው የቢዝነስ ምቹ ከባቢ አለመኖር ነው፡፡ ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ከመንግሥት አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መንግሥት ለጀማሪዎች ሼድ ይሰጣል፤ብድር ያመቻቻል ነገር ግን ጀማሪዎች ወደ አነስተኛ ኤንተርፕራይዝ ሲያድጉ መንግስት ድጋፉን ይቀንሳል፡፡ ለምን አንደ ሆነ ግልጽ አይደለም ሲሉ የጣቶቹን ተግዳሮት የሚጀመርበትን ሂደት ደ/ር ሐሰን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ በአጠቃላይ ትልቁን የስራ ዕድል ሊፈጥር የሚችለውን ክፍል መንግሥት ትኩረት አልሰጠው ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

ስለዚህ በመንግሥት እና በአነስተኛ እና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች ያለው ዝምድና መስተካከል አለበት ይላሉ፡፡ 2ኛው ከሰዎችነ አመለካከት እና ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም በአገራችን የኤንተርፕራይዞች የሚጀመሩት እንደመተዳደሪያ ሥራ እንጂ ለረዠም ጊዜ ታስቦ ለድውልድ የሚተላለፍ ድርጅት ለማቆም አይደለም፡፡ ይሄ በራሱ ኤንተርፕራይዞቹ በፍጥነት አንዳይስፋፉ በምክንያትነት ይነሳል፡፡ ስለዚህ በሥራ ፈጠራ ላይ አስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት የሥልጠና እና የትምህርት ሥርዓታችን ጀምሮ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ 3ኛ ብድር አለመኖር ነው፡፡ ይሄ በጣም ሥር የሰደደ ችግር ነው፡፡ ለዚህ ችግር መንግሥት አንድ መፍትሔ ማበጀት አለበት፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ ጥዋት ከእንቅልፋችን ስንነቃ ስለ ወጣቱ ሕብረተሰብ ማሰብ የሁላችን አሃላፊነት ነው ብለዋል፡፡

ዋናው የወጣቶቹ ስብዕና ላይ ለውጥ ማምጣት ስለሆነ አንደ አዲስ ቻምበር ያሉ ንግድ ምክር ቤቶች እና ሌሎች ባለድርሻዎች ወጣቶቹ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ የሜተርሺፕ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል፡፡ በውይይቱ ላይ በርካታ ጥያቄዎችን እና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን በአቅራቢዎች በኩል ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡


Coming Soon Events
14TH ADDIS CHAMBER INTERNATIONAL AGRICULTURE & FOOD TRADE FAIR
14ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የእርሻና ምግብ ንግድ ትርዒት
አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER
14th AGRIFEX
14TH
AGRIFEX ETHIOPIA
"Maximizing Value Additions through Agro Business"
Food processing
2ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የሜዲካል እና ፋርማሲቲካል ንግድ ትርኢት
THE 2ND ADDIS CHAMBER INTERNATIONAL
MEDICAL & PHARMACIUTICAL TRADE FAIR
2nd MED
ይቻላል
It's Possible!
PUBLIC PRIVATE PARTNERSHIP
FOR ENHANCED MEDICAL SERVICES

# በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የወጣት ስራ ፈላጊዎችን ጥያቄ ለመመለስ ሁሉም ባለ ድርሻ ሊረባረብ እንደሚገባ ተገለጸ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

የተቀናጀ የወጣቶች ፕሮጀክት ወይንም ከፍታ በስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ ላይ የንግድ ለንግድ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር ልዩ አማካሪ ነቢያ መሀመድ በኢትዮጵያ የወጣቱ የህብብረተሰብ ክፍል ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥር ይይዛል ፤ ይህውም 70 ሚሊየን ይሆናል ብለዋል ፡፡ ወጣቱ ትልቅ ሀብትና አቅም መሆኑን ጠቁመው ይህንን የወጣት ሃይል በአግባቡ ከተጠቀምንበት ትልቅ ሃብት ነው ብለዋል፡፡

ለዓመታት ለወጣቶች የሚፈጠር የስራ እድል አልነበረም ያሉት ነቢያ፤ ይህም ሊሆን የቻለው ሀገሪቱ ካለችበት ድህነትና ኃላቀርነት እና ተያያዥ ምክንያቶች የስራ አጡ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ሊሆን ችሏል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በየአመቱ 2 ሚሊየን ወጣት ስራ ፈላጊ ወደ ገቢያው እንደሚገባ አንስተው ፤ ይህንን ስራ ፈላጊ ወጣት ወደ ስራ ካላስገባነው እድል ሳይሆን ጥፋት ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡

መንግስት ይህንን ወጣት ወደ ስራ እንዲገባ ኃላፊነትም ግዴታም አለበት ያሉት ወ/ሮ ነቢያ የግሉ ዘርፍ የበለጠ ሚና መጫወት ይኖርበታል ሲሉ አሳሰበዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው በያመቱ 3 ሚሊየን ስራ ለወጣቱ ለመፍጠር ግብ አስቀምጠን ወደ ስራ ገብተናል ያሉት አማካሪዋ ወ/ሮ ነቢያ ፤ ይህውም ገበያው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ከማዘጋጀት ጀምሮ ፤ የሚፈጠረው የስራ እድል ዳቦ መብላት መሆን አለበት ብለን እየሰራን ነው፡፡ ሆኖም የብድር አቅርቦት ፣ የገቢያ ትስስር ፣ የመሰሪያ ቦታ ፣ የመሸጫ ቦታ ችግሮች ትልቅ ክፍተት መሆናቸውን ጠቅሰው ፤ ይህንን ችግር ለመፍታት የስራና ክህሎት ሚንስቴር የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርፆ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በግሉ ዘርፍና በመንግስት መካከል አንደ አገናኝ ድልድይ በመሆን የግሉን ዘርፍና የማህበረሰቡን ጉዳዮች በማንሳት ግንዛቤ ማሳደግ የንግድ ለንግድ ትስስር በመፍጠር ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ለአነስተኛና ጥቃቅን ልምድ ማካፍልና ማብቃት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በሀገራችን ስራ ፈጣሪዎች ሲመሩ ቆይተው ፤ ለወጣቱ የማስተላለፍ ነገሮች ቢኖሩም ወጣቱ በእውቀትና በክህሎት ሳይዘጋጅ ድርጅትን እንዲመራ ድርጅቱን ለውድቀት መዳረጉ አይቀሬ ነው ያሉት አቶ ዘካሪያስ አሰፋ የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሀፊ ፤ በዚህም ምክንያት ስኬታማ የተባሉ የቢዝነስ ሰዎች ለልጆቻውም ሆነ ለሌሎች ስራተኞች ኃላፊነታቸውን ካስተላለፉ በኃላ ስኬታማ መሆን ተስኖት ሲወድቅ ይታያል ብለዋል፡፡

በመሆኑም ወጣቱን በማነፅ ፣ ድርጅት የመምራት ብቃቱ እንዲጎለብት የማብቃት ስራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ምክር ቤቱ ወጣትና ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎችን የሚደግፍ የቢዝነስ ማበልጸጊያ ማዕከል ፕሮጀከት ይፋ ማድረጉን ጠቅሰው ፤ ስልጠናዎችን መሰጠት ፣ የገቢያ ትስስር መፍጠርና የስራ ፈጣሪነት ባህልን ማሳደግ እንዲሁም ስራ ፈጣሪዎች ያለባቸውን የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ ፕሮጀክቱ ወደ ስራ መግባቱን ገልፀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ አገሪቱ ማሳካት የምትፈልገው ከዘላቂ ልማት ጋር የተጣጣመና የስራ ፈጠራና የቢዝነስ-ምህዳሩን ለማስፋት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የተቀናጀ የወጣቶች ፕሮጀክት በስራ እድል ፈጠራ ፣ በኢኮኖሚ እገዛ ፣ በጤና ፣ በሲቪክ እና ለወጣቶች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በ18 ከተሞች ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡

በወጣቶች ንቁ ተሳታፊዎች ላይ የሚሰራው ይህ ፕሮጀክት ለአምስት አመት የሚቆይ ሲሆን ከመንግስት እቅድና ኢንቨስትመንት ጋር የተጣመረ ነው ብለዋል፡፡ በወጣቶች የሚመሩና የሚተዳደሩ ቢዝነሶችን ለመደገፍ የሚያስችሉ በርካታ የፕሮጀክት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ፡፡የንግድ ትስስር ወይንም ቢዝነስ ቱ ቢዝነስ መድረክ ለቢዝነስ ጀማሪ ወጣቶች እንዲሁም ቢዝነስ ለመጀመር ሃሳብ ላላቸው ወጣቶች ልምድና ተሞክሯቸውን ፤ የሄዱበትን መንገድ አካፍለዋል፡፡

በንግድ ለንግድ ትስስርና ውይይት መድረኩ ላይ በዶሮ እርባታ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ፣ በቆዳና ሌጦ ዘርፍ ፣ የተሰማሩ ስኬታማ ወጣቶች ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡

የንግድ ለንግድ መድረኩ ዋና አላማም ሞዴል የቢዝነስ ድርጅቶችና ወጣቶች መካከል ግንኙነት እና ትስስር ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡

እንደዚሁም የወጣቶችን የስራ እድል ለይቶ ለማወቅና ለገቢያ ቅልጥፍና አስተዋፆ በሚሆን መልኩ ወጣቶች የራሳቸውን ስራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ጭምር መሆኑን በመድረኩ ላይ ተገልፃል ፡፡

# ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ሀገራዊ ስጋት እንደሆነ ተገለጸ

ሙስና፤ግልፅነት የጎደለው የቀረጥ እና የግብር አሰራር መኖሩ የጥቁር ገበያው መበራከት በአንዳንድ አስመጪዎች እና ላኪዎች የሚፈጸሙት በሃሰተኛ ደረሰኞች ማጭበርበር ለሕገወጡ የገንዘብ እንቅስቃሴ ዋና ዋና ምክንያቶች አንደሆኑ ተመልክቷል፡፡

ለምሳሌ በፈረንጆቹ 2018 ወደ 3 ቢሊየን የሚሆን የአሜሪካን ዶላር በሕገወጥ መንገድ እንደወጣ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 80 በመቶ የሚሆነው በሃሰተኛ የዋጋ ደረሰኞች አንደተወራረደ ተገልጿል፡፡

ከወጪ ንግዳችን ሌላ የምንዛሬ ምንጭ የሆነው በውጪ ከሚኖሩ ኢትዮጰያውያን ወደ አገር ቤት የሚላከው ገንዘብ ነው፡፡ ይህ በውጪ ምንዛሬ መልክ የሚገባው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ እና አንዳንዴም ከአገሪቱ አመታዊ የኤክስፖርት ገቢ ከፍ ያለ ነው፡፡ ነገር ግን እስከ 5 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር የሚደርሰው ይኸው ገንዘብ እስከ 80 በመቶ የሚሆነው የሚገባው በጥቁር ገበያ አዘዋዋሪዎች በኩል ነው ሲሉ ጥናት አቅራቢው አቶ ይርጋ ተስፋዬ ተናግረዋል፡፡ 90 በመቶ የሚሆነው የውጪ ምንዛሬ ገንዘብ ወደ ውጪ የሚወጣው በተጓዥ መንገደኞች አማካኝነት እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

የውጪ ምንዛሬ እጥረት መኖሩ፤ ጠንካራ የገንዘብ ፍሰት ቁጥጥር አለመኖር ከሕጋዊው የምንዛሬ ተመን ይልቅ የጥቁር ገበያ ምንዛሬ ከፍተኛ መሆኑ ለሕገወጥ ዝውውሩ ገፊ ምክንያቶቸ ናቸው ተብሏል፡፡ የብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች የሕግ ማስከበር ተቋማትን የቁጥጥር አቅም ማሳደግ፤የቀረጥ አና የግብር ሰብሳቢ መ/ቤቶች አሰራራቸውን ማዘመንእና በቅንጅት መሥራት፤ በባንኮች እና በጥቁር ገበያው መካከል ያለውን የምንዛሬ ተመን በማጥበብ ተወዳዳሪ እንዲሆን መሥራት ከመንግሥት ይጠበቃል የሚሉት ምክረሃሳቦች በጥናቱ ተሰንዝረዋል፡፡

ለጥናቱ ማዳበሪያ ይሆን ዘንድ ከውውይቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ሃሳቦች እና አስተያየቶች ተነስተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በብሔራዊ ባንክ፤በፋይናንስ ደሕንነት ፤በጉምሩክ እና በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች መካካል ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጉ እና በቅንጅት አንዲሰሩ ማገዝ ፤ በድንበር አካካባቢ ቁጥጥር ማጠናክር እና ከጎረቤት አገራት ጋር በትብብር መሥራት፤ ለሕብረተሰቡ እና በትምህርት በቶች ጭምር ስለ ሕገወጥ ገንዘብ ዘውውር አስከፊነት ትምህርት መስጠት ፤ ከውጪ የሚላኩ የቤተሰብ ሀዋላዎች ሕጋዊ መስመር እንዲከተሉ የሚያስችሉ አሰራሮች መዘርጋት ያስፈልጋል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

# የግልግል ዳኝነት እና ጥቅሙ ... እውነትም ግልግል ፤ ለተከራካሪዎች እስከ 4 ጊዜ ያህል ለዕርቅ ዕድል ያመቻቻል

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የንግድ ሥራ አንደ ማንኛውም በሰዎች የቃል ስምምነት የሚከወን ዕለታዊ ሥራ ነው ብንል ከአውነታው ብዙ አንርቅም፡፡ ንግድ የሚከወነው በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የሚከናወን ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ በገዢ እና በሻጭ ባቅራቢ እና በተቀባይ መካከል የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት ሲፈጠር ያኔ የንግድ ሂደቱ ባለበት ይቆማል፡፡

ንግድ በባሕሪው የሚጀመረውም የሚከናወነውም በተግባቦት ነው፡፡ የአዲስ አባባ ንግድ ም/ቤት በአገራችን ትልቁ የነጋዴውን ሕብረተሰብ በጋራ የሚያስተባብር አና የነጋዴው የጋር ድምጽ ነው፡፡

ምክር ቤቱ የንግዱን ሕብረተሰብ ለመደገፍ በርካታ አገልግሎቶች ከምሥረታው ጀምሮ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል ወቅታዊ የቢዝነስ መረጃዎች፤ የገበያ እና ንግድ ትርዒቶችን፤ ለግሉ ዘርፍ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል > >>

# መልካም ተሞክሮ ፤ የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ ትብብር በአነስተኛና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች





**(በይድነቃቸው ዓለማየሁ)**

በአገራችን በአነስተኛ እና መካከለኛ ኤንተርፕራይዝ ሥራ አጥ ወጣቶችን በየአካባቢው በመመልመል ሥራ የተጀመረው በ1997ዓም እንደነበር ይታወሳል፡፡ አነስተኛ ተብለው የሚመደቡት ገና ጀማሪዎቹ ሆኑ በአብዛኞቹ ሰርቶ ለመለወጥ ትልቅ ሕልም ያላቸው ወጣቶች ናቸው፡፡ እነርሱም ከ 5 በታች የሆኑ ሠራተኞችን የሚያቅፉ ትናንሽ ቢዝነሶች ናቸው፡፡ መካከለኛዎቹ ደግሞ ከ5-200 የሚሆኑ ሰዎችን ቀጥረው በተሻለ ቴክኖሎጂ እና ካፒታል የሚንቀሰቀሱ ናቸው፡፡

ሁለት አስርት አመት ሊሞላው ጥቂት የቀረው የአነስተኛ እና መካከለኛ ንግድ ዘርፍ ዛሬ ላይ ሲታይ ባለበት የሚሄድ ይመስላል፡፡ ለዚህ ብዙ ጥናት እና ምርምር የሚያሻው አይመስልም፡፡ የዛሬ 18 ዓመት ገደማ ሲቋቋሙ፤ ለምሳሌ በብረታብረት ሥራ ተሰማርተው በርና መስኮት በማምረት የጀመሩት ዛሬም በርና መስኮት እያመረቱ ነው፡፡ በብሎኬት እና በሲሚንቶ ውጤቶችም ላይ የሰተማሩትም ቢሆኑ አሁንም እዛው ናቸው፡፡ ስኬታማዎቹ ቁጥራቸው ያነሰ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ያሉበት ደረጃ ያኔ እንደተፈጠሩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ መንግሥት ለእነዚህ አነስተኛ እና መካከለኛ አንቀሳቃሾች ነጻ የመሥሪያ ቦታ(ሼድ)፤ነጻ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረቡ ማለፊያ ነው፡፡ ነገር ግን ከውጪ ማሽኖችን አስመጥተው ሥራቸውን ማስፋትና ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ እንዳይሸጋገሩ ለማሽነሪ መግዣ የሚሆን ብድር ማግኘት የሰማይን ያህል ይርቃቸዋል፡፡

ዛሬ ዛሬ ላይ ዘርፉን ለመታደግ በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ ትብብር አንዳንድ መልካም ጅማሮች እየታዩ ነው፡፡ መንግሥት የመስሪያ ቦታ እና የሊዝ ካፒታል ሲያቀርብ የግሉ ዘርፍ ደግሞ ወጣቶቹ ለሥራ የሚፈልጉትን ማሽነሪዎች በማቅረብ የሚሳተፉበት አሰራር መጀመሩ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ ዓላማም በግሉ እና በመንግሥት ትብብር በተጀመረው ሥራ የተሳተፈ አንድ ወጣት ሥራ ፈጣሪ እና አንድ ባለሃብት ተሞክሮ ላይ ተመስርቶ ለሌሎች ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች መረጃ ለማካፈል ነው፡፡ በዚህ አንጻር ለአስተኛ ኢንተርፕራይዞች መንግሥት ከሚያደርግላቸው ድጋፍ ጎን ለጎን ለአነስተኛ ሥራ ፈጣሪዎች ብቻ ማሽኖችን እና መለዋወጫዎች እንዲሁም ተዛማጅ ሥልጠና በማቅረብ ድጋፍ የሚያደርጉ የግል ድርጅቶች አንዱ ኤልዳድ የተባለው ማሽን ፤መለዋወጫ እና ሰልጠና አቅራቢ ደርጅት ነው፡፡



የኤልዳድ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ አወቀ አሥራት እንደሚሉት ሥራ ፈጣሪዎች በባንኮች እና በማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ብድር ለመግኘት ያለው ውጣ ውረድ ሩቅ ህልም የነበራቸውን የብዙዎች ባለ ራዕይ ወጣቶች ተስፋ ያስቆረጠ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ይህን የፋናንስ ክፍተት ለመሙላት ድርጅታቸው ከሊዝ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በገባው ውል መሠረት ለወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ፤ለኢትዮጵያ ከባቢ ሁኔታዎች ምቹ እና ጥራታቸውን የጠበቁ ማሽነሪዎች እና ተዛማጅ መለዋወጫዎችን ያቀርባል፤ይተክላል፤ስልጠና ይሰጣል፤ ይከታተላል፡፡

አቶ አወቀ እንደሚሉት ወደ እርሳቸው የሚመጡት ወጣቶች የሚፈልጉት የሥራ ዘርፍ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ በሳይንሳዊ የሥራ ፈጠራ ዘዴ ወጣቶቹ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን ዘርፎች በማሳየት ፤ ወጣቶቹን በስነ ልቦና አበርትተው ያመኑበትን የሥራ ዘርፍ መርጠው እንዲሰማሩ ይመክራሉ፡፡ ብዙዎቹ መነሻ ገንዘብ እንኳን ሳይኖራቸው በጋለ የሥራ ፍላጎት ወደ ድርጅታቸው እንደሚመጡ እና የምክር አገልግሎት በነጻ እንዲያገኙ ባለሙያ ይመደብላቸዋል፡፡

ሁላችንም እንደምንረዳው አብዛኞቹ ወጣቶች የመነሻ ካፒታል የሚያገኙት ከቤተሰብ፤ከዘመድ በሚገኝ ትንሽ ገንዘብ ነው፡፡ “በወፌ ቆመች” ደረጃ ላይ ያሉ ወጣቶች ለብድር ማስያዣ የሚሆን ቤት ወይም መኪና ከየት ሊያመጡ እንደሚችሉ ሲታሰብ በራሱ የሚያስገርም ነው፡፡ ይኸው የብድር ዋስትና ችግር በሌሎች አገራትም ያለ የዘርፉ ችግር ነው፡፡ ሌላው የአነስተኛ እና መካከለኛ ዘርፉን አላላውስ የሚላቸው በጨረታ ሚያገኙት ሥራዎች በቂ ማሽነሪዎች ፤በቂ የሰው ሃብት ችግር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት እነዚህ ኤንተርፕራይዞች ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ሌላው መንግሥት ለዘርፉ በቂ ትኩረት አለመስጠት እና ክትትል አለማድረጉ ነው፡፡

ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመላ ኢትዮጵያ በተከፈቱት የካፒታል ዕቃ አቅራቢዎች(የሊዝ ፋይናንሲንግ ተቋማት ) ከግሉ ዘርፍ ጋር ትሥሥር በመፍጠር ሥራ ፈጣሪዎች በቀላሉ ማሽነሪዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ወጣቶቹ እንዲደርሳቸው የሚያደርግ አሰራር ተጀምሯል፡፡

ከመንግሥት እና የግል ትብብር ተጠቃሚዎች መካከል ወጣት አንተነህ ደግፌ አንዱ ነው፡፡ ወጣት አነተነህ በሙያው መሐንዲስ ሲሆን የሚፈልገውን ሥራ ለመጀመር አንቅፋት ሆኖ ለአመታት ያስቸገረው ነገር ቢኖር የመነሻ ገንዘብ ነው፡፡



ገንዘቡስ ተገኝቶ ለሥራው የሚያስፈልገው ማሽነሪ ማግኘት ደግሞ የሩቅ፤ ሩቅ ነበር፡፡ ነገር ግን መንግሥት ባመቻቸው የሊዝ ፋይናንሲንግ አግባብ በተመቻቸለት ድጋፍ እና ከኤልዳድ ኩባንያ በተሰጠው የቴክኒክ ምክር፤ድጋፍ፤ የምስማር ማምረቻ ማሽነሪ እቅርቦት በ2አመታት ጊዜ ውስጥ ሕልሙ እውን አንደሆነለት ይናገራል፡፡ ከደረሰበት ስኬት ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረድ እና ትዕግስትን የሚጠይቁ ፈተናዎችን እንዳለፈ የሚናገረው ወጣት ሥራ ፈጣሪ ዛሬ ላይ ወደ 20 ለሚጠጉ ወገኖች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

ይህን መሳይ የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ ትብብር ለወጣቶች ትልቅ እፎይታ የሚሰጥ እና ህልማቸውን እውን የሚያደርጉበት መልካም አጋጣሚ ነው ይላሉ፡፡ ኩባንያቸውም የመነሻ ገንዘብ ያላቸው እና በግላቸው ሥራ ለመጀመር አስበው ነገር ግን በምን ሥራ ላይ ለመሰማራት ለመወሰን የሚቸገሩ ወጣቶችን ጭምር በነጻ የማማከር አገልግሎት እንደሚሰጥ ይናገራሉ፡፡ እርካታ የሚገኘው ትርፍ በማግኘት ሳይሆን ወጣቶቹ ድርጅታቸው የሚሰጠውን ሥልጠና ወስደው፤ክህሎታቸውን አዳብረው፤በማሽኖቹ ሰርተው ብድራቸውን ከፍለው አድገው እና ለመገኖቻቸው የሥራ ዕድል ሲፈጥሩ ማየት ነው ይላሉ ወጣቱ የኤልዳድ ኩባንያ ሥራ አሥኪያጅ፡፡ በአዲስ አበባም ይሁን በመላ አገሪቱ የሚገኙ ወጣቶች በዚህ አዲስ ዕድል እንዲጠቀሙ ለመጠቆም እንወዳለን፡፡ ሰላም!!

# ወጣቶችና ቢዝነስ፤‘ወጣትነት እንደ አበባ ነው!’

**በካሳሁን ማሞ**

ወጣትነት ጉልበት ነው፡፡፡ ወጣትነት የስራ ሰአት ነው ፡፡ ወጣትነት ስጋት የምንላት የቢዝነስ ስሌት ብዙም ቦታ የማታገኝበት ይልቅስ ለስራ የምንደረደርበት አፍላ ወቅት ነው ፡፡ በእርግጥ ማንም ሰው ኩባንያ አቋቁሞም ሆነ ራሱ ሲመራው ቆይቶ ወደ ወጣቱ ትውልድ ማስተላለፉ በአገራችን የተመለደና የመጣንበትም አካኼድ ነው፡፡ነገር ግን በቀጣይ የኩባንያውም ሆነ የሀገር ስኬታማነት ምን ያኽል ነው ብለን ስንጠይቅ ለጥያቄያችን አርኪ መልስ የምናገኘው ከስንት ስንት ነው?
ጉዳዩ ወጣቱን ትውልድ ለሥራው ብቁ አድርጎ ከማዘጋጀት ጋር የተያየዘ ነው፡፡ ወጣቶች ዕውቀትና ልምዱ ካላቸው የኩባንያንም ሆነ የሀገርን ሸክም እንደማቅለል ይቆጠራል፡፡ ችግሩ እኛ ታላላቆች ኩባንያንም ሆነ ሀገርን ከመራን በኋላ በስተ እርጅና የደረሰ ወጣት ካለ በዕውቀትና በክህሎት ሳይዘጋጅ ወጣት ስለሆነ ብቻ ድንገት ኩባንያውንም ሆነ አመራሩንም የማውረስ ነገር አለ፡፡ ልብ አድርጉ ወጣቱ እንደ ታላላቆቹ የለፋበት አይደለም ፡፡ ድንገት እጁ ላይ ጠብ ያለ ንብረት ወይም ሀገር ነው፡፡ የራዕዩም አካል ሳይሆን ስለሚችል ሊያበላሸው ይችላል፡፡ በአብዛኛው ስኬታማ የሚባሉ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል > >>

# የውጪ ምንዛሬው በገበያ ከመሆኑ በፊት ቀዳሚ ሥራዎች አሉ፡፡

መንግሥት በቅርቡ የፋይናንስ ዘርፉን ለገበያ ክፍት እንዲሆን መወሰኑን ተከትሎ የዚሁ አካል ነው የሚባለው የካፒታል ገበያ ሥርዓት ለመጀመር ዝግጅት እየደረገ መሆኑ ይሰማል፡፡ ሌላው ቀሪ ሥራ ሆኖ የሚታሰበው ደግሞ የውጪ ምንዛሬ ተመን ከመንግሥት እጅ ወጥቶ በገበያ እንዲወሰን ማድረጉ ነው ፡፡ በቀላል አነጋገር የውጪ ምንዛሬ ተመን በገበያ ይወሰን ሲባል በእንግሊዝኛው (Floating) የዶላር እና ሌሎች የውጪ አገር ገንዘቦች በብር የሚመነዘሩበት መጠን በጨረታ ይወሰን እንደማለት ነው፡፡ የብዙ አገራት ልምድ እንደሚያሳየው የፋይናንስ ዘርፋቸውን ለውጪ ገበያ በከፈቱ ማግስት የማያባራ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ በእኛም አገር ነገር ይዋል ይደር እንጂ መሆኑ ምንዛሬው በገበያ እንዲመራ መደረጉ አይቀሬ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ የውጪ ምንዛሬ በገበያ የሚመራበት ሥርዓት በብዙ አገራት የተለመደ አሰራር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተለይ 1990ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ በዓለም ባንክ እና የዓለም ገንዘብ ድርጅት እንደኛ ባሉ ድሃ አገራት በሚያደርጉት ጫና የፋይናንስ ዘርፋቸውን ለውጪ ባንኮች የከፈቱ አገራት ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ ከድጥ ወደ ማጡ የገቡ ፤ሌሎቹ ደግሞ አንደ ወረርሽኝ ገብቶ የወጣለቸው ፤ ጥቂት የሚባሉት አገራት ደግሞ በለስ የቀናቸው እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በእኛም አገር ከዚህ የአገራት ልምድ ጋር ተያይዞ የተለያዩ እሳቤዎች ይንጸባረቃሉ፡፡ አንደ ጀማሪነታችን ሁሉ አንዳንዶቹ የምንዛሬ ተመን ለገበያ መከፈት የለበትም ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ሁኔታዎች እየታዩ ቀስ በቀስ አንክፈት ባይ ናቸው ፡፡ የቀሩት ወገኖች ደግሞ " ህልም ተፈርቶ …" እንዲሉ አሁኑኑ ይከፈት እና ችግሮችን ተጋፍጠን እንለፋቸው ይላሉ፡፡

ይህንን አነጋጋሪ ጉዳይ አስመልክቶ የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት አንድ ጥናት በማስጠናት ሰሞኑን ከባለድርሻዎች ጋር ውይይት አዘጋጅቶ ነበር፡፡ በቀረበው ጥናት መሠረት በዓለም ላይ የሚሰራባቸው 3 ዓይነት የውጪ ምንዛሬ አተማመን መንገዶች አሉ፡፡ እነርሱም በማዕከላዊ የመንግሥት ባንክ የሚወሰን፤በጨረታ የሚወሰን እና ሌላው ደግሞ እንዳስፈላጊነቱ በመንግሥት/በማዕከላዊ ባንክ እና በገበያ የሚወሰን አሰራሮች ናቸው፡፡ የውጪ ምንዛሬ ግብይታቸውን ወደ ገበያ ሥርዓት ያሸጋገሩ በተለይ የአፍሪቃ እና የእስያ አገራትን ተሞክሮዎች በጥናቱ የተዳሰሱበት ነበር፡፡ የአገራችን የምንዛሬ ተመን የሚወሰነው መንግሥታዊ አካል በሆነው በብሔራዊ ባንክ ነው፡፡ እ.ኤ.አ 1990ዎቹ ጀምሮ የውጪ ምንዛሬ ተመን በየጊዜው መንግሥት እየጨመረ እንደነበር እና በዚያው ልክ የብር የመግዛት አቅም እየወረደ ሲሄድ እንደነበር ጥናቱ አስታውሶ በተለይ እ.ኤ.አ ከ2018 ዓም ጀምሮ መንግሥት ባደረጋቸው ተከታታይ የውጪ የምንዛሬ ተመን ማሻሻያዎች፤ የአገራችን ብር ከአሜሪካን ዶላር ጋር የነበረው የምንዛሬ ንጽጽር፤ ማለትም የእኛ ብር የአሜሪካን ዶላርን የመግዣ አቅም እስከ 68% እንደወረደ አመልክቷል፡፡ አሁን ላይ ለሚታየው የውጪ ምንዛሬ ተመን ጣሪያ መንካት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ከተባሉት መካከል የወጪ ንግዳችን ደካማ መሆኑ፤የንግድ ሚዛን ጉድለታችን እየሰፋ መሄዱ፤ የተንሰራፋው የሕገወጥ የገንዘብ ዘውውር፤ የደራው የጥቁር ገበያ ፤ በሰሜኑ ክፍል የነበረው ጦርነት ፤ በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶች፤ ገንዘብ ወደ ውጪ ማሸሽ፤ ጠንካራ የገንዘብ ፍሰት ቁጥጥር ሥርዓት አለመኖር፤ በድንበር አካባቢዎች ጥብቅ ቁጥጥር አለመኖር ፤ አሳሪ የሆኑ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፤ እንዲሁም የዋጋ ንረቱን መቆጣጠር አለመቻሉ የሚሉት በጥናቱ ተዘርዝረዋል፡፡ ጥናት አቅራቢ የነበሩት አቶ ኢያሱ ኩመራ በተለይ ወደ ውጪ አገራት ገንዘብ ማሸሽን አስመልክተው ባለፉት 10 አመታት ወደ 45 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር የሚጠጋ ሃብት ከአገራችን በተለያዩ መንገዶች ወደ ውጪ እንደወጣ የፐ/ር ዓለማየሁ ገዳን ጥናት ዋቢ አድርገው ገልፀዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተው የውጭ ምንዛሬ እጥረት መባባስ አሁንም የሚያባራ አይመስልም የሚሉት አቶ ኢያሱ ዛሬ ላይ በሕጋዊው የምንዛሬ ተመን መሠረት 1 ዶላር በአማካይ በ54 ብር ሲመነዘር በጥቁር ገበያው ደግሞ አስከ 100 ብር ይመነዘራል ብለዋል፡፡

እስከ 73% ድረስ የውጪ ምንዛሬ የሚገኘው ከወጪ ንግዳችን ሲሆን ይህም በአመት የምናስገባው ከ4 ቢሊየን ዶላር አይበልጥም ፤ ሌላው ምንጭ ከውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የምናገኘው ሲሆን እርሱም ካለፉት 10 አመታት በአማካይ እስከ 16 % ቀንሷል ሲሉ አቶ ኢያሱ ተናግረዋል፡፡




ከውጪ ከምናስገባው ይልቅ የምናወጣው ዶላር እጅግ የበለጠ ነው፡፡ ለአብነትም ባለፈው የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከኤክስፖርት የተገኘው ገቢ ወደ 1 ቢሊየን ዶላር ገደማ ሲሆን በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለኢምፖርት ደግሞ 4 ቢሊየን ዶላር ገደማ ወጥቷል፡፡

እሰከ ዛሬም ድረስ ዝቅተኛውን የውጪ ምንዛሬ ተመን የሚወስነው መንግሥታዊው ብሔራዊ ባንክ ሲሆን ባንኩ ባለፉት 10 አመታት ውስጥ ከውጪ ምንዛሬ ጋር በተያያዘ 29 የሚሆኑ መመሪያዎችን አውጥቷል፡፡ በመንግሥት በኩል የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም የውጪ ምንዛሬ እጥረቱ እየተባባሰ ፤ የብር የመግዛት አቅሙም ከቀን ወደ ቀን እየወረደ እንጂ የሚረጋጋ አይመስልም ሲሉ ተመራማሪው ይሞግታሉ፡፡

የውጪ ምንዛሬ በገበያ ሲወሰን ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል የወጪ ንግድ ያበረታታል፤

ወደ ገጽ 11 ዞሯል > >>



# የግልግል ዳኝነት እና ጥቅሙ...

<<< ከ ገጽ 6 የዞረ

ሥልጠናዎች፤ የንግዱን ሕብረተሰብ መብት ጥቅሞች እንዲከበሩ በነጋዴው እንዲሁም በመንግሥት መካከል አገናኝ ድልድይ በመሆን የፖሊሲ አድቮከሲ ሥራዎችን ይሰራል፡፡ በተለይም በንግድ ሥራ ላይ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በቀላሉ የግልግል ዳኝነትን በመጠቀም ምክር ቤቱ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት በተለይ በነጋዴዎች መካከል ይሁን በነጋዴዎች እና በሌላ ወገኖች መካከል የሚፈጠሩ ውዝግቦች ከመደበኛ ፍ/ቤት በተለየ በአጭር ጊዜ እና ቀጠሮ ተከራካሪ ወገኖች በግልግል ዳኝነት (Arbitration) ሁለቱም ወገኖችን የሚያስማማበት ሥራ የሚያከናውነው በራሱ የግልግል ተቋም ነው፡፡

በዚህ እትም የግልግል ተቋም ባለፉት 9 ወራት ውስጥ ያከናወናቸውን የግልግል ዳኝነት እና ሌሎች ድጋፎችን አስመልክቶ በአጭሩ ለአንባቢያን ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡ ንግድ ቢያንስ በሁለት ወገኖች መካከል ይከናወናል፡፡

ታዲያ የንግድ ሥራ ሕይወት የሚኖረው የግብይት ሲኖር ነው፡፡ ግብይቶች ሁሉ በስምምነት አያበቁም፤ አንዳንዴ አለመግባበቶች ይፈጠራሉ፡፡ ግብይት ባሕላችንም ከመኖሪያ ቤት እና ጥቂት ንብረቶች በቀር ግብይት የሚፈጸመው በቃል ስምምነት ነው፡ ለምሳሌ የከብት ፤የእህል ወይም የሌላ ግብይቶች የሚከናወኑት 3ኛ ወገኖች ጣልቃ ገብተው ሻጭ እና ገዥን በዋጋ እንዲቀራረቡ እና እንዲስማሙ በማድረግ ግብይቶች እንዲፈጸሙ ያግዛሉ፡፡ ነገር ግን ከትናንሽ ግብይቶች እስከ ትላልቆቹ አብዛኛውን ጊዜ ግብይቶች በገዥ እና በሻጭ መካከል በሚደረግ ውል ሳይሆን በቃል ስምምነት ነው፡፡

በቃል ስምምነት ስለሚከናወን ንግድ የሕግ ባለሙያው እና የምክር ቤቱ የግልግል ተቋም ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ዮሐንስ ወ/ገብርኤል እንደሚሉት በንግድ ሥራ ላይ እንደ ሽያጭ፤ብድር፤ዋስትና የመሳሰሉት የሚከናወኑት በሁለት ወገኖች መካከል በሚደረግ መግባባት ነው፡፡

የአገራችን ሕግም በቃል ስምምት ለሚደረግ ግብይት እውቅና ይሰጣል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ገዝ እና ሻጭ ሳይገናኙ በኤሌክትሮኒክ (online) አማካኝነት ይካሄዳል፡፡ በጣም ጥቂት የሚባሉ የተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ግብይታቸው በውል ይፈጸማል ይላሉ፡፡



እንግዲህ የተቋሙን እንቅስቃሴ ስንመለከት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአጠቃላይ 20 ጉዳዮችን በግልግል ፤ 9 ጉዳዮችን በድርድር፣ 5ቱን በጊዜያዊ የግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ አድርጓል፡፡ 54 ለሚሆኑ አባላት የህግ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በጋራ በመሆን የጨረታ ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚሟላት 37 ለሚሆኑ ድርጅቶች የኦዲት ሰነዶችን የማረጋገጥ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም የግልግል ተቋሙን የግልግል፣ አጁዲኬሽን፣ ማስማማት/ ማግባባት የአስተዳደር ክፍያዎችን አሁን ካለው ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር በማጣጣም ማሻሻያ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን ይሄንን ስራ ለማከናወን ኮሚቴ ተቋቁሞ በአሁኑ ሰአት ኮሚቴም ስራውን በማጠናቀቅ አጸድቆ ስራ ላይ አውሏል፡፡

**የዲጂታል አገልግሎት መጀመር**

በግልግል ተቋሙ የሚስተናገዱ ደንበኞችን ተቋሙ ድረስ በተለያየ ምክንያት መገኘት ባይችሉ በአይቲ የተደገፈ ሂደት ጉዳያቸውን እንዲቀጥሉ ለማስቻል ባቀድነው መሰረት ለምስክሮች ዙም ሚቲንግን በመጠቀም ባሉበት ሀገር ሆነው እንዲመሰክሩ በማስቻል ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ እንዲያልቁ አስችለናል፡፡

የሰነድ ልውውጦችን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከተለመደው አሰራር ወጣ በማድረግ በኢሜል፣ በሶሻል ሚዲያዎች በመጠቀም አሰራሩን ቀልጣፋ ማድረግ ያቀድን ሲሆን ደንበኞች፣ ዳኞች የሚፈልጉትን ሰነዶች ምልልሶች በዘመናዊ መልኩ በመለዋወጥ የስራ ጊዜው እንዲያጥር ማድረጉን አቶ ዮሐንስ ገልጸዋል፡፡ የአሰራር ግልጽነት እና ተጠያቂነት፡ የግልግል ተቋሙ የሚመራበት 5 ሕግጋት /በሚዲያዎች አሉ፡፡ እነዚህ ተከራካሪ ወገኖች ምን ምን አሟልተው መምጣት እንዳለባቸው ፤ምንያህል የአገልግሎት፤ የአስተዳደር እና ለዳኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በዳይሬክተሮች ቦርድ የጸደቁ ናቸው፡፡ እነዚህንም ደንበኞች በግልፅ እንዲያውቁት እናደርጋለን ብለዋል፡፡

**ነጋዴዎች የግልግል ዳኝነትን (Arbitration)ለምን ይመርጣሉ?**

ነጋዴዎች/ኩባንዎች አለመግባባቶች ሲያጋጥማቸው ወይም ውዝግብ ውስጥ ሲገቡ ከመደበኛ ጉዳዩ ከመደበኛ ፍ/ቤት ይልቅ ወደ ግልግል ዳኝነት የሚመጡት ምክንያቶችን ሲያብራሩ በመደበኛ ፍርድ ቤት መንግሥት መሠረተ ልማቱን፤የሰው እና የቁሳቁስ እና አስፈላጊው ሃብት እና ቁሳቁስ የሚመድበው መንግሥት ነው፡፡ ዳኛውን መንግሥት ነው የሚሾመው፤ መሠረተ ልማቱን የሚያሟላው መንግሥት ነው፡፡ ነገር ግን አንድ አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተከራካሪ ወገን ዳኛ የመምረጥ መብት የለውም፡፡ ዳኛውን መንግሰት ይመድባል፡፡ ነገር ግን በግልግል ዳኝነት ገላጋይ ዳኞች የሚሰየሙት በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ነው ፡ ፡ ይህም ተከራካሪ ወገኖች በዳኞቹ ገለልተኛነት፤ችሎታ እና ብቃት ላይ እምነት ሲኖራቸው ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውጥ በተቋሙ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት በቀር ሌላ ስልጣን የለውም፡፡ ይህ በራሱ በሁለቱም ወገኖች ፍትሃዊ ውሳኔ እንደሚያገኙ በውስጣቸው እምነት እንዲያሳድሩ እና የንግድ ግንኙታቸው በቶሎ ተቋጭቶ ፤ ወደ ነበረበት ተመልሶ ፤ሁለቱም ወገኖች ቢዝነሳቸው እንዲመለሱ ስለሚረዳቸው ነው ይላሉ ዳይሬክተሩ፡፡ ሌላው ንግድ የማይነካው የሙያ ዘርፍ የለም፡፡ ስለዚህ ውዝግቦቹም ከተለያዩ የሙያ እና የውዕቀት መስኮች ጋር የተያያዙ ሆነው ይመጣሉ፡፡ ለምሳሌም የምህንድስና፤ የኬሚካል፤የኢንሹራንስ ፤ግብርና ወዘተ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴም ከውል የሚመነጩ ውዝግቦች ይመጣሉ፡፡ ስለዚህ በፍርድ ቤት የሕግ ባለሙያዎች አንጂ በእያንዳንዱ ሙያ ዘርፍ ላይ ዝርዝር እውቀት ያላቸው የዳኞች ስብስብ አይገኝም፡፡ ነገር ግን በአዲስ ቻምበር የግልግል ተቋም በተለያዩ ዘርፎች ላይ እውቀቱ ያላቸውን ዳኞች ዝርዝር የያዘ መዝገብ አለ ፡፡ በዚህ መሠረት አንደ ክርክሩ ዘርፍ ታይቶ ለዘርፉ ቅርብ የሆኑ ዳኞች ይመደባሉ ፡፡

**ቀጠሮ አና ምልልስ፡**

ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይልቅ የግልግል ዳኝነት ነጋዴዎች የሚመርጡበት ሌላው ምክንያት በአጭር የቀጠሮ ጊዜ ውስጥ ክርክሮች እልባት ማግኘታቸው ነው፡፡ ትልቁ ቀጠሮ ከ6 ወር አይበልጥም፡፡ ስለዚህ በእነዚህ አና በሌሎች ነጋዴው ምቹ በሆኑ አገልግሎቶች የግልግል ተቋሙን ተመራጭ ያደርገዋል ይላሉ አቶ ዮሐንስ፡፡

አዲስ ቻምበር የሚሰጠው የግልግል ዳኝነት ለአባላቱ ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱን ለሚጠይቅ አባል ላልሆኑ ግለሰቦች እና ኩባንያዎች ጭምር ነው፡፡ ሌሎች አገልግሎቶችንም እንዲሁ፡፡

በአገር ውስጥ ለሚነሱ ንግድ ነክ ውዝግቦች አንደ አዲስ ቻምበር ባሉ የግልግል ተቋማት ወሳኔ ሲያገኙ በሌላ በኩል ድንበር የለሽ እና ዓለማቀፋዊ ንግድ በሆኑ ጉዳዮች በዓለማቀፍ የግልግል ተቋማት አማካኝነት ይፈታሉ፡፡ ለምሳሌ በሁለት አገራት በሚገኙ ኩባንያዎች እና ኩባንያዎች ወይም ደግሞ በኩባያዎች እና በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ አካልላት መካካል ለሚነሱ የቢዝስ ውዝግቦች ወይም የይገባኛል ጥያቄዎች እንደ ፐርማነንት ኮርት ኦፍ አርቢትሬሽን እና አይ.ሲ.ሲ.ኢንተርናሽናል ኮርት ኦፍ አርቢትሬሽን የሚባሉት የዓለማቀፍ የግልግል ተቋማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡



ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች ወደ አዲስ ቻምበር የግልግል ተቋም ሲመጡ መጀመሪ ጉዳያቸው በተቋሙ መታየት እንደሚችል ይታያል፡፡ ይህም በተከራካሪ ወገኖች መካከል ውል ካላቸው በውላቸው ላይ አለመግባባት ቢፈጠር በግልግል አለያም በሌላ ተመሰሳይ መንገድ እንዲፈታ ተገልጾ ከሆነ፤ አልያም በውላቸው ላይ ባይገለጽም በአዲስ ቻምበር የግልግል ተቋም እንዲያገኙ ከተስማሙ ፤ ወደው እና ፈቅደው ውል ገብተው የግልግል ዳኝነት አገልግሎታቸንን እንዲያገኙ እናመቻችላቸዋለን የሚሉት ከፍተኛ የሕግ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ሚስጥር መሐመድ ናቸው፡፡

**የደንበኞች ምስጢር አጠባበቅ እና የአግልግሎት እርካታ**

የግልግል ተቋሙ የደንበኞችን ምስጢር ይጠብቃል፡፡ ለዚሁም አሰራር ሥርዓት አለ ፡፡ በግልግል ዳኝነቱስ ምን ያህል ተከራካሪ ወገኖች እርካታ ያገኛሉ? ለሚለው ጥያቄ የግልግል ተቋሙ በየ6ወሩ ግብረ መልሶችን እና መረጃዎችን ያጠናቅራል፡፡ በጠቅላላው ወደ 90 በመቶ የሚሆኑት ጉዳዮች በተቋሙ በሚሰጠው ውሳኔ ረክተው ግንኙነታቸውን የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ ወደ እኛ የሚመጡት ጉዳዮች የሚታዩት ባለሙያ በሆኑ ዳኞች ስለሆነ ወደ ይግባኝ የሚሄዱ በጣም ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ ሲሉ ከፍተኛ የሕግ ባሙያዋ ገልጸዋል፡፡

# አዲስ ቻምበር የቢዝነስ ማበልፀጊያ...

<< < ከፊት ገጽ የዞረ

ፕሮጀክቱ ይፋ ሲደረግ ንግግር ያደረጉት የስራና ክህሎት ኮሚሽን ሚኒስትር ደኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን ሥራ አጥነት በኢትዮጵያ ቅድሚያ የሚሰጠው የማክሮ ኢኮኖሚ አጀንዳ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን፣ በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን ያህል አዳዲስ ሥራ ፈላጊዎች ወደ ሥራ ገበያው እንደሚቀላቀሉ ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም ተቋማቸው ከሥራ ፈጠራ ጋር በተገናኘ ያለውን ክፍተት በማጥናት ብሔራዊ የድርጊት እቅድ በማዘጋጀት በየዓመቱ ሦስት ሚሊዮን ያህል ሥራዎች በመፍጠር፣ እ.ኤ.አ. በ2030 ለአስር ሚሊዮን ዜጎች ዘላቂ የስራ እድሎች እንዲፈጠሩ ዕቅድ መያዙን አቶ ንጉሱ አመልክተዋል ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው ሥራ አጥነትን ለመቅረፍና እና በኢትዮጵያ የሥራ ፈጠራን ለማስፋፋት ቁልፍ ከሆኑት ስራዎች ውስጥ አንዱ ሥራ ፈጣሪነት ( ኢንተርፕርነርሽፕ ) መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

በመሆኑም ንግድ ምክር ቤታቸው ከአውሮፓ ህብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የቢዝነስ ፈጠራ ማዕከል በማቋቋም ወጣት ስራ ፈጣሪዎች ፣ እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርራይዞች ስልጠና በመስጠት ፣ የገቢያ ትስስር በመፍጠር ማዕከሉ ያሉባቸውን ችግሮች የሚፈታ ይሆናል ብለዋል ፡፡

ፕሮጀክቱ የስራ እድልን ለመፍጠር ፣ እድገትና ብልፅግና ለማረጋገጥ እንዲሁም ፈጠራንና የሰራተኛ ቁጥርን ለማሳደግ ኢትዮጵያዊያን ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችንና አነስተኛ አና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማበልጸጊያ ስነ -ምህዳር የማጠናከር ውጥን አለው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የቢዝነስ ፈጠራ ማዕከሉ በግብርና ዘርፍና እንዲሁም ግብርናውን እና ቴክኖሎጂውን በማጣመር ግብርናና ቴክኖሎጂ ዘርፎች የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ስራ ፈጣሪ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ ስራ ይሰራል ብልዋል ፡፡

ንግድ ምክር ቤቱ ከአውሮፓ ኅብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ያቋቋመው የአራት አመት ፕሮጀክት ሲሆን ድህነትንና ሥራ አጥነትን በመዋጋት የኢትዮጵያን የንግድና የኢኮኖሚ ምኅዳር በመለወጥ ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ወ/ሮ መሰንበት ተናግረዋል፡፡

# ወጣቶችና ቢዝነስ፣‘ወጣትነት እንደ አበባ ነው!’...

<< < ከ ገጽ 6 የዞረ

ኩባንያዎች ለወጣት ልጆቻቸውም ሆነ ለሌሎች ካወረሱ በኋላ ሥራው እንደ ቀደምቶቹ ዘመን ወርቃማነቱን ይዞ ሲቀጥል አይስተዋልም፡፡ በውርስ ከማስኬድ ይልቅ በኩባንያ አመራር ክህሎቱና ዕውቀቱ እንዲኖራቸው ማድረግ ተቀዳሚ ስራቸው መሆን ነበረበት ፡፡

በነገራችን ላይ የሁሉም የወጣትነት ዘመን የራሱ የሆነ ወርቃማ ሊባል የሚችል አጋጣሚ አለው ብዬ አስባለው፡፡፡ ለአብነት አሁን ባለው ሁኔታ የዓለማችን ሕዝብ በአብላጫው ዓለም አቀፋዊ ሆነና ከዚኽ ቁጭ ተብሎ ዋሽንግተን፣ ኒውዮርክና በሌላውም ዓለም እየተከናወነ ያለውን ድርጊት በእፍታው ወደምናውቅበት የቴክኖሎጂ ዘመን ላይ ደረስን፡፡ ዓለም ትንሽ መንደር ኾነች ተባለ፡፡ ነገር ግን የጋራና ዋነኛው ገዥ ሀብት ሆኖ አረፈ፡፡

“…ሀብት ካለኽ የሆነ ትርጉም ያለው ሰው ነኽ፤ ከሌለህ ደግሞ የለህም፡፡” የሚለው የጋራ ዜማ መሆን ጀመረ፡፡ በአንዳንዱ የዓለማችን ክፍል መማር ትልቅ ክብርና ቦታ አለው፡፡ በአንዳንዱ ዘንድ ደግሞ ሀብት የበለጠ ክብር አለው፡፡ በምዕራቡ ዓለም የሰው ሚዛን “…ምን ተማረ ሳይሆን ምን ይዞ ተገኘ?” የሚለው ነው፡፡ ወደ ኋላ ሔደን የእኛን አገር የቆየ ባህል ብናስታውስ “ምን ተምሯል?” በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ያ ስሜትና ዕምነት እየወረደ ቁሳዊ ሀብት የበላይ እየሆነ የመጣበትን እውነት እያየን ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በየከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ እየተማረ ያለው አብዛኛው ወጣት ዕውቀቱን ቢጨብጥም ባይጨብጥም በኾነ መንገድ ተመርቆ ስለመውጣት የሚያልም፤ ዕውቀቱ ኖረም ቀረም የተሰጠችኝን ፈተና ብቻ ልለፋት’ና ሌላው የራሱ ጉዳይ የሚል አስተሳሰብ የያዘ መኾን ለዚህች አገር አሳሳቢ ነው የሚል ዕምነት አለ፡፡

አንድ ተማሪ ከትኛውም ትምህርት ተቋም ተመርቆ ሲወጣ ሌላው ቢቀር ርዝራዥ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ ፈተናውን ለማለፍ ብቻ አይደለም፡፡ፈተናውን በተፈተንክ ቁጥር ትንሽ ዕውቀት አጠራቅመህ ትወጣለህ ነው ዓላማው እንጂ የተፈተንከውን ሁልጊዜ ታስታውሳለህ ማለት አይደለም፡፡ ሳታውቀው አብሮ የሚዘልቅ ዕውቀት ይዘህ ትወጣለህ ለማለት ነው፡፡

አሁን ፍርሃት እየሆነብን ያለው አብዛኛው ሰው ትምህርትንና ዕውቀትን የማንነቱ መለኪያ በማድረግ ፈንታ የምማረው ትምህርት ገንዘብ እስካመጣልኝ ድረስ ሌላው ትርፍ ነው ለሚል አስተሳሰብ እየተገዛ መምጣቱ ነው፡፡ ይኼ ዓይነቱ ወጣት ትኩረቱና ሩጫው ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ ማሰስ ብቻ ይሆንና ሕጋዊና ሕገ ወጡን መንገድ እንዳሻው እየቀላቀለ ሊዋኝ ነው፡፡

ይኼ ያስፈራል፡፡ በአቋራጭ መክበር ማለት “…ገንዘብ ላግኝ እንጂ ገንዘቡ የሚገኝበት ሒደት እንዳሻው ቢኾን አይገ’ደኝም፡፡” እንደ ማለት ነው፡፡ ይኼ ጉዳት አለው፡፡ አብላጫው የአዲሱ ዘመን ወጣት ባለ ሀብት በዚያ አስተሳሰብ ውስጥ መምጣቱ ራሱን እንደ ስኬታማ ሰው እንዲቆጥር ያደርገዋል፡፡ የተደጋገመ ውሸት የእውነት ያኽል ይቆጠራልና ትውልዱም ይኼን “ስኬት” በሚል ለመኮረጅ ሲራኮት ይታያል፡፡

በአቋራጭ መንገድ ኺያጁም እንደ ጀግናና እንደተሳካለት ሰው ተቆጥሯልና ቀጣይ ሕይወቱም ያው በመጣበት ሕገ ወጥነት የተቃኘ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ራሱን ብቻ ሳይሆን አገርን ሁሉ እያበላሸ ይቀጥላል፡፡ በአቋራጭ ወደ ሀብቱ ሠገነት ለመድረስ የምንጠቀምበት ሒደት ያሰብነውን ያመጣልን ይሆናል፡፡ነገር ግን ሀብትና ሥልጣን ያለ ዕውቀት አደገኞች ናቸው፡፡

በዚያ መንገድ ሚሊየነር የኾነ ሰው በማኅበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነውን የቤተሰብ ሕይወት እንኳን መምራት ሲቸግረው ይታያል ምክንያቱም ሀብቱን ያገኘበት መንገድ ለየት ያለ ስለሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ቀናና ምቹ ያልሆኑ ድርጊቶችን ቢያከናውን ግድ የለውም፡፡ እየተፍጨረጨረም ቢኾን ትክክለኛውን መንገድ የያዘ ባለ ሀብት ያገኛት እሴት የብዙ ድካም ውጤት መኾኗን አሳምሮ ያውቃል፡፡ የድካሙን ውጤት ወደ ቀጣይ እርከን ለማሸጋገር መክፈል ያለበትን ዋጋና የሚጠብቀውንም ድካም ያውቃል፡፡

ስለዚህ ኹሌም ይማራል፡፡ ብዙም ርቀት ይጓዛል፡፡በአንድ ጊዜ አገር ጉድ ያሰኘ ሚሊየነር ላይሆን ይችላል ነገር ግን ሕይወቱ በየዕለቱ በእርካታ የተሞላች ትኾናለች፡፡ ሕይወት በገንዘብ ብቻ የምትተመን ከኾነ ዋጋዋ ዝቅ እያለ ይኼዳል፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ደስታችንን በገንዘብ ብቻ መለካት የለብንም፡፡“…የፈለገው ይኹን፡፡ ለዚህም ለዚያም አቅምኼ… ብቻ ቶሎ ልክበር፡፡” የሚሉ ወጣቶች ልክ እንደ አበባ ናቸው፡፡ አበባን ከቀረጥከው በኋላ ለአራትና አምስት ቀን ያህል ያምራል፡፡ ሲሸትም መዓዛው ልዩ ነው፡፡ ግን ቶሎ ይከስማል፡፡ ይወድማል፡፡ ምክንያቱም ከምንጩ ተቆርጧል፡፡ ከዋናውና ከትክክለኛው ሥፍራ ሊመጣ የሚችለው ውሀና ምግብ፤ ሊያሳድገው የሚችለው ንጥረ ነገር ተቋርጧል፡፡ ተፈጥሯዊ ዕድገቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሳይቆረጥ የሚፈልገውን ውሀ እያጠጡና እየተንከባከቡ ውበቱ ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ከተያዘ እየፋፋ፣ እያፈራና እየተስፋፋ ይኼዳል፡፡ ወጣትነትም እንዲሁ ነው፡፡

ወጣቶች ባለ ራዕይ እንዲሆኑ ሀገርን እና ድርጅታቸውን እንዴት እንደሚያሳድጉ ኩባንያቸውና ሀገራቸው የት መድረስ እንዳለበት ተሻጋሪ አስተሳሰብ እንዲያመጡ እንፈልጋለን፡፡ ‘ዛሬ ተኮር’ ብቻ ከሆኑ በጥቃቅን ነገሮች ይዋጣሉ፡፡ በራዕይ የሚመሩ ወጣቶች ብዙ አይደሉም፤ እንዲበዙ ግን ምኞታችን ነው፡፡ የእያንዳንዱ ሰውና አገር የመጀመሪያው ትልቅ ኃላፊነት ቤተሰብ ነው፡፡ አገር የሚሆነው የቤተሰብ ጥርቅም ነው፡፡ ቤተሰቡን እና ወጣት ልጆቹን በአግባቡ መርቶ ወደ ስኬት ያላመጣ አገር እና ቤተሰብ አለኝ ቢለን አይገባንም፡፡ ወጣቱ እያንዳንዱ ቀን በከንቱ እንዲያልፍበት መፍቀድ የለበትም፡፡ ‘ትናንት’ እንደገና አይመጣም፡፡

ዛሬ እዚህም ሆነ ስራችሁ ቦታ የተገኛችሁት አዲስ ነገር ለመሥራት እንጂ ትናንት የሠራችኋቸውን ነገሮች ለመደጋገም አይደለም፡፡ በየዕለቱ፣በየሰዓቱና በየደቂቃው አዳዲስ ነገሮች መፈጠር አለባቸው፡፡ አዳዲስ ነገሮች የሚፈጠሩት ደግሞ ከችግር ውስጥ ነው፡፡ ለስራ ሲባል ጠያቂ ወጣት ቢኖር እንድንሻሻል ያደርግናል፡፡ ስለዚህ ወጣት ለስኬት እና ለእድገት ሲባል በጥፍር ማቆም የሚችል አቅም ያለው መሆን አለበት፡፡

ተገዳዳሪ ሃሳብየሚያቀርብ፤ስትናገርም ስትሠራም አማራጭ የሚያቀርብ ወጣት መኖር አለበት፡፡ አዛውንቱም ቢሆን በሃሳብ የሚገዳደረው ሰው እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ የቢዝነስ ባለቤቶችም ሆነ መሪዎች የወጣቶችን ችግር ብንፈታላቸው ቢያንስ መጪው ጊዜን ብሩህ እንዲሆን ያስችላል፡፡

ታላላቆች እና የቢዝነስ ባለቤቶች አረኞች ነን ብለን የምናስብ ከኾነ ከብቶቹ፣ በጎቹ፣… እንዲያዩን ማድረግ አለብን፡፡ እየተደበቅን እረኛ መሆን አንችልም፡፡ ‘ራሳችንን ለወጣቶች ቅርብ ማድረግ አለብን፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ያለፈ ማህበረሰብ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ ሲሆን አላየንም፡፡፡

እርግጥ ነው! የወጣቶቻችን የሥራ ባሕል እየተለወጠ ስለ መሆኑ አበረታች ነገር እያየን ነው፡፡ ጠዋት ከእንቅልፉ ተነስቶ “ቁርሴን አክስቴ ቤት እበላለሁ፡፡…ገንዘብ ከአጎቴ እወስዳለሁ…” በሚል ወጣት ፈንታ “…ካልሠራሁ በስተቀር ገንዘብ አላገኝም፡፡ መብላትም መኖርም አልችልም፡፡” የሚሉ እየበረከቱ ነው፡፡ አሁን ግን “ካልተሠራ ምንም ነገር አይቻልም፡፡” በሚል ሥነ-ልቦና የተቃኘ እንቅስቃሴ እያየን ነው፡፡ ይኼ መጠናከር አለበት፡፡

# የውጪ ምንዛሬው በገበያ ከመሆኑ...

<< < ከ ገጽ 8 የዞረ

የአገራትን ተቀማጭ ምንዛሬ መጠን ያሳድጋል፤ የሕገወጥ የገንዘብ ምንዛሬ እና ዝውውርን ይከላከላል የሚሉት ይገኙበታል። ምንዛሬ በገበያ ሲወሰን ጉዳቶች እና ጥቅሞች አሉት፡ ነገር ግን ወደ አገራችን ስንመለስ በአገራችን ያለውን የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን አስቀድሞ መልክ ማስያዝ እንደሚያስፈልግ ሌላው ወረቀት አቅራቢ አቶ መላኩ ታንኩ አሳስበዋል። በዚህ መሠረት ከሁሉ በፊት የውጪ ንግዳችንን በዐይነት እና በጥራት ማሳደግ፤የኮንተትሮባንድ ንግድን መቆጣጠር፤ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፤ የንግድ ሚዛን ጉድለቱን ማጥበብ ፤ የዋጋ ግሽበቱን መቆጣጠር እና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች መከናወን አለባቸው ሲሉ ምክረሃሳባቸውን ሰንዝረዋል። ብሔራዊ ባንክ የሚከተለው የምንዛሬ ስርዓት የገበያ እና የመንግሥት ቁጥር ያለበት ወይም በእንግሊዝኛው (ሚክስድ) የሚባለው አይነት ነው ቢልም በተግባር ግን አሁንም ድረስ አንደ ዓለም ገንዘብ ድርጅት ያሉት ተቋማት ብሔራዊ ባንኩ ጠንካራ የምዛሬ ተመን ቁጥጥር ያደርጋል ባዮች ናቸው።

መሬት ላይ ያለው እውነታ ሲታይ በአገር ውስጥ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ፍላጎት መኖሩን እና የምንዛሬ አመልካች ነጋዴዎች ምላሽ የሚያገኙት ወራት አንዳንዴም አመታትን ጠብቀው በሬሽን እንደሆነ ይታወቃል። አሁንም እያደገ የሚሄደው የውጭ የምንዛሬ ፍላጎት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚሟላ አይመስልም። ሌላው ችግር ያለችው ውስን የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት እንኳን አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ቅድሚያ ሰጥቶ የመመደብ አሰራር አይታይም። እነዚህ እና ሌሎች ምክንያቶች ተደማምረው የጥቁር (ትይዩ) ገበያው እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል ሲሉ አቶ መላኩ ያስረዳሉ። የሌሎች አገራትን ልምድ አስመልክቶ እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ በዓለም ባንክ እና በዓለም የገንዘብ ድርጅት አማካኝነት ብዙ አገራት የመዋቅር ማሻሻያ በሚል መርሃግብር የፋይናስ ዘርፋቸውን ለገበያ ክፍት አድርገው የውጪ ምንዛሬያቸው በገበያ እንዲመራ ሲፈቅዱ በመጀመሪያ አካባቢ ችግሮች ያስተናገዱ ቢሆንም ማክሮ ኢኮኖሚያቸው ተረጋግቶ ቆይቷል። የወጪ ንግዳቸው መጠን እንዲጨምር ፤ የንግድ ጉድለታቸው ደግሞ ሊቀንስ ችሏል። ከእነዚህ መካከል ጎረቤት ኬንያ፤ጋና ኡጋንዳ እና ቻይና ይገኙበታል። በተቃራኒው ሌሎቹ ደግሞ እንደ ናይጀሪያ፤ሩሲያ ኡዝቤክስታን እና ሱዳን ያሉ አገራት ለብዙ ጊዜ በቀውስ ውስጥ ቆይተው በኋላ ኢኮኖሚያቸው አንዳንሰራራ በጥናቱ ተመልክቷል።

አሁን ላይ በኢትዮጵያ የሚታየው የምንዛሬ ሥርዓት ሕጋዊው እና ሕገወጡ የምንዛሬ ጎን ለጎን እየሄዱ ነው። በሁለቱ መካከል ያለው የምንዛሬ ልዩነትም ከ100 % በላይ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። በሕጋዊ እና በሕገ ወጡ መካከል እንዲህ የሰፋ ልዩነት መኖሩ በራሱ የከፋ የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል ሲሉ አቶ መላኩ ሥጋታቸውን ገልጸዋል። ልዩነቱ ሊሰፋ የቻለውም በግጭቶች ሳቢያ ገንዘቦች በሕገወጥ መንገድ በመውጣታቸው፤ የባንኮች የጥቁር ገበያውን ለመከላከል የሚያስችሉ ጠንካራ አሰራሮች አለመኖር ፤ ላለፉት 2 አመታት በሰሜኑ ክፍል የዘለቀው ጦርነት እና ትላልቅ የሜጋ ፕሮጅክቶች የምንዛሬ ፍላጎት መጨመር ፤ የጥቁር ገበያው እንዲደራ ያደረጉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው። የሆነ ሆኖ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ የምንዛሬ ተመን በገበያ አንዲወሰን ማድረጉ እንደማይቀር የታወቀ ነው የሚሉት አቶ መላኩ ዋናው ጉዳይ እንዴት እና መቼ ይከፈት በሚለው ጉዳይ ላይ ብዙ ማሰብ ይገባለናል ሲሉ ይሞግታሉ።



የውጪ ምንዛሬ ተመን በገበያ አንዲወሰን ካስፈለገ መንግሥት ሊከሰቱ የሚችሉትን ቀውሶችን ታሳቢ በማድረግ እና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎች እና መዋቅራዊ ዝግጅቶች ማድረግ አለበት። ነገር ግን የምንዛሬ ሥርዓቱ ለገበያ ክፍት መቼ ይሁን ለሚለው ጥያቄ አቶ መላኩ ሲመልሱ ሁኔታዎች ደረጃ በደረጃ እየታዩ፤ መንግሥት የቅርብ፤የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ መርሃግብር አውጥቶ ቀዳሚ ሥራዎች ካከናወነ በኋላ ወደ ገበያ ቢሸጋገር ይሻላል ሲሉ ምክረሃሳባቸውን በመሰንዘር ሃሳባቸውን የአጠቃልለዋል።

በጥናቱ ላይ በርካታ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ከታዳሚዎች የተሰነዘሩ ሲሆን በአቅራቢዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። ከቦታው ተገኝተው ጥናቱን መከታተል ያልቻሉ አባላትን በማሰብ በእኛ ከአንባቢያን አንዲመች አድርገን የተወሰኑትን አቅርበናል።

"... ያለችው ውስን (የውጪ ምንዛሬ) ሃብት በቁጠባ ከመጠቀም ይልቅ ቅድሚያ ለማይሰጣቸው ጉዳዩች ቅድሚያ ሲሰጥ ይስተዋላል። ይሄ በራሱ አንዱ ችግር ነው ማለት ይቻላል።"

አስፋው ወ/ገብርኤል (ከአዋሽ ባንክ)



አንድ ዘወትር የምንሰማው አባባል አለ። የፋይናንስ ዘርፉን ለውጪ ገበያ ክፍት ብናደርግ ያለብንን የውጪ ምንዛሬ እና ሌሎቹንም ተያያዥ የፋይናንስ ችግሮች ይፈታል የሚል ነው። በአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት እና በፋይናንሻል ሊበራላይዜሽን መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አይመስለኝም።

የፋይናነስ ዘርፉን ገበያ መር በማድረግ ኢኮኖሚውን ያሳደገ አገር የለም። ስለዚህ የፋይናን ዘርፉ እና አጠቃላይ የአገራችን የኢኮኖሚ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል። የውጪ ባንኮች ቢገቡ ለአገራችን ኢኮኖሚ ሳይሆን ለራሳቸው እድገት ነው የሚሰሩት። ነገር ግን የውጭ ምንዛሬ እጥረቱ እንዳለ ሆኖ ያለችውን ውስን ሃብት በቁጠባ የመጠቀም ነገር አይታይም። ቅድሚያ ለማይሰጣቸው ጉዳዩች ዶላር ሲሰጥ ይታያል። ይሄ በራሱ አንዱ ችግር ነው ። ሌላው ከውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት የሚገኝ ዶላር ነው ።

"በኒውዮርክ ዓለም ገበያ ላይ 1ቶን ቡና 3ሺህ 6መቶ ዶላር ይሸጣል። አገር ውስጥ በኢ.ሲ.ኤክስ 1ቶን ቡና 3ሺኅ 8 መቶ ዶላር ይሸጣል። ስለዚህ በ1ኮንቴይነር ቡና ላኪዎች ከ600 አስከ 1ሚሊየን ብር እየከሰሩ ነው የሚሸጡት።"

አብዱልቃድር (ከሕብረት ባንክ)



"ኤክስፖርት ማሳደግ" በተደጋጋሚ ሲነገር እንሰማለን። ኤክስፖርታችን ለምን አላደገም ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው ። ምክንያቱም ስለማያዋጣ። ብዙ ሰው ለምን ወደ ኢምፖርት ይገባል ካልን ደግሞ መልሱ አሁን ባለው ሁኔታ ኢምፖርት ማድረግ ኤክስርት ከመሥራት በተሻለ ስለሚያዋጣ ነው።

ስለዚህ በኤክስፖርት ላይ ገበያ ካለ ኤክስፖርቱ ያድጋል። ለምሳሌ ዛሬ ወይም ትናንት የዓለም ገበያ የቡናን ዋጋ አንመልከት ። ዛሬ በኒውዮርክ የዓለም ገበያ ላይ 1ቶን ቡና ዋጋ 3ሺህ 6መቶ ዶላር ይሸጣል። ነገር ግን እዚህ አገራችን ላይ ኢ.ሲ.ኤክስ ቨርቲካል ትሥሥር የሚል አሰራር ተጨምሮ 1 ቶን ቡና እዚሁ አገር ውስጥ 3ሺሕ 8መቶ ዶላር ያወጣሉ። ስለዚህ በ1 ኮንቴይነር ቡና ላኪዎች ከ600 አስከ 1ሚሊይን ብር እየከሰሩ ነው የሚሸጡት። ይሄንን ጉዳይ መንግሥትም የሚያውቀው ነው። አጠቃላይ ኤክስፖርት ለምን የማያዋጣ ሆነ፤ ለምን ኢምፖርት ያዋጣል ብለን ብንጠይቅ። የችግሩ መነሻ ዶላር የምንገዛበት በትክክለኛ የገበያ ዋጋ አለመሆኑ ነው። ምክንያቱም ዶላሩን በርካሽ እየተገዛ ኢምፖርት ይደጋል። ስለዚህ ኢምፖርተሮች ትርፋማ እየሆኑ፤ ኤክስፖርቱ እየቀጨጨ በመሄድ ላይ ነው። በእኔ ግምት የዶላር ምንዛሬ በገበያ እዲመራ ቢደረግ፤ የዶላር ምንዛሬ መጠን በገበያ ዋጋ ይወሰናል። ስለዚህ ዶላር ፍለጋ ወደ ጥቁር ገበያ የሚሄድ ሰው አይኖርም። ይህ ደግሞ ኤክስፖርተሮችን ያበረታታል። መንግሥት ከውጪ ብዙ ዶላር ለመሳብ ሲል በተደጋጋሚ ዲቫሉዌት (የአንድ ዶላር፤ በብር ምንዛሬ መጠን ) በተደጋጋሚ ከፍ ሲያደርግ ቆይቷል። ነገር ግን ዲቫልዌሽን ማድረግ እስከዛሬ ድረስ ለችግሩ መፍትሔ አላመጣም።

"ኤክስፖርታችን አድጎ ፣በቂ የውጪ ምንዛሬ አመንጭቶ፣ ዳጎስ ያለ ክምችት አግኝተን ወደ ገበያ ለመሄድ የሚለው ሃሳብ በጣም ሩቅ ነው።"

አቶ ዘላለም ከብሔራዊ ባንክ



የውጪ ምንዛሬ በገበያ እንዲወሰን የሚደረገው ዋናው ዓላማ ኤክስፖርትን ለማበረታታት ነው። በተመሳሳይ ኢምፖርትን በመቀነስ የንግድ ሚዛን ጉድልታችንን ለማሻሻል ነው። ሊበራላይዜሽን በራሱ ይህንን ችግር የሚቀርፍ ነው። ኤክስፖርታችን በቂ የውጪ ምንዛሬ አመንጭቶ ፤ ዳጎስ ያለ ክምችት አግኝተን ወደ ገበያ ለመሄድ የሚለው ሃሳብ በጣም ሩቅ ነው።

አገራችን ከፍተኛ የውጪ ዕዳ ያለባት አገር ናት። ከጠቅላላ አገራዊ ምርት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ከኤክስፖርታችን ጋር ሲታይ ትልቅ ትርጉም ይሰጣል። ስለዚህ ከዚህ የዕዳ ጫና መውጣት የምንችለው ኤክስፖርታችንን በማሳደግ ነው። አለያም ዜጎች ከውጪ ወደ አገር ቤት ከሚልኩት የውጪ ምንዛሬ ፤ በብድር እና እርዳታ መልክ በሚገኝ ውጪ ምንዛሬ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ገበያውን መክፈት አይደለም መታሰብ ያለበት ፤ከተከፈተ በኋላ ለሚፈጠሩ ችግሮች ብልሃት ማበጀት ላይ ጥናቱ ትኩረት ቢሰጥ ጥሩ ነው።

ሌሎች ተጨማሪ ሃሳቦች እና ትችቶች ከተሳታፊዎች የተሰነዘሩ ሲሆን በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ ንግድ ምክር ቤቱ የጥናቱን አጠቃላይ ግኝት ለፖሊሲ ማሻሻያ ግብዓት ይረዳ ዘንድ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል ተብሏል።